fetena.net : Ethiopian online exams and textbooks



ሒሳብ

የተማሪ መጽሐፍ

2ኛ ክፍል

አዘጋጅ፡-
ከፈለኝ ወልደዮሃንስ

አርታኢ፡-
ገብረየስ ኃይለጊዮርጊስ

ገምጋሚዎች፡-
ዳኛው አስማረ
ክፍሌ ይልማ



ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

AL GHURAIR
PRINTING AND PUBLISHING LLC

ምስጋና

የዚህ መጽሐፍ ዲዛይን ህትመትና ስርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ኘሮጀክት (ሀሕሀሓ) አማካኝነት ነው። የኘሮጀክቱ ዋና ዓላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው።

የኢትዮጵያ ፌዲራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ለGEQIP የዋለውን ገንዘብ ያገኘው በብድር/በእርዳታ ሲሆን ብድሩን/ እርዳታውን የሰጡት ዓለምአቀፍ የልማት ማህበራት (IDA)፣ ፋስት ትራክ ኢንሼትቭ ካታሊቲክ ፈንድ (FTI CF) እና ሌሎችም የልማት አጋሮች ማለት የፊንላንድ፣ የኢጣሊያ የልማት ማህበር፣ የኔዘርላንድና የታላቋ ብሪታኒያ የእርዳታ ድርጅት አለምአቀፍ የልማት ዋና ክፍል (DFID) ናቸው።

ሁሉንም በዝርዝር መጥቀስ የማይቻል በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ይህ የተማሪ መጽሀፍና የመምህር መምሪያ እውን እንዲሆኑ ያልተቆጠበ ድጋፍቸውን ሰጥተዋል። በዚህም ትምህርት ሚኒስቴር ምስጋናውን ያቀርባል።

© በኢትዮጵያ ፌዲራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር

1ኛ እትም፣ 2004 ዓ.ም

ISBN 978-99944-2-223-4

የአል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት
የፖ.ሳ.ቁጥር 5613
ዱባይ፣
የተባበሩት የአረብ ኤሜሬት

ከኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር
የፖ.ሳ.ቁጥር 100767
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ጋር በመተባበር ይህን መጽሐፍ ለኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅተው አትመው፣ አሰራጭተዋል።

ሁሉም የህትመት መብቶች ተከብረዋል።
የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም እንደማይቻል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዲራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የኮፒራይትና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ 10ኛ አመት ቁጥር 55 አዲስ አበባ ጁላይ 19/2004 ይከለክላል።

የስዕሎችን የኮፒ ራይት መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

ማውጫ

ገፅ

የምዕራፍ 1:- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ

1.1 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ክለሳ 1
1.2 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ ክለሳ..... 5
1.3 ባለ አንድ አሃዝ ቁጥርን ከባለ ሁለት አሃዝ ቁጥር ጋር ያለ አለኝታና ያለብድር መደመርና መቀነስ 8
1.4 ባለ አንድ አሃዝ ቁጥርን ከባለ ሁለት አሃዝ ቁጥር በአለኝታ እና በብድር መደመርና መቀነስ 10
1.5 ሁለት ባለ ሁለት አሃዝ ሙሉ ቁጥሮችን ያለ አለኝታ እና ያለ ብድር መደመር እና መቀነስ..... 11
1.6 ሁለት ባለ ሁለት አሃዝ ሙሉ ቁጥሮችን በአለኝታ እና በብድር መደመር እና መቀነስ..... 13
1.7 በመደመር እና በመቀነስ እስከ 100 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች የሚሰሩ የቃላት ኘሮብሌሞች 14
የምዕራፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች 15

ምዕራፍ 2:- ማባዛትና ማካፈል እስከ 100

2.1 ያለ ቀሪ በ2 እና በ10 ማባዛትና ማካፈል ክለሳ..... 16
2.2. በ0 እና በ1 ማባዛት እና ለ1 ማካፈል 24
2.3. ማባዛትና ማካፈል በ3፣4፣5፣6፣7 ፣8 እና 9..... 26
የምዕራፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች 44

ምዕራፍ 3:- ልኬት

3.1 ርዝመትን በሳንቲ ሜትርና በሜትር መለካት..... 45
3.2. በሳንቲ ሜትር እና በሜትር የተገለፁ ርዝመቶችን መደመርና መቀነስ..... 46
3.3 ይዘትን በሊትር መለካት 48
3.4 በሊትር የተገለፁ ይዘቶችን መደመርና መቀነስ..... 50
3.5 ክብደትን በኪሎ ግራም መለካት..... 52
3.6 በኪሎ ግራም የተገለፁ ክብደቶችን መደመርና መቀነስ 52
የምዕራፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች 55

ምዕራፍ 4:- የክፍልፋዮች ፅንሰ-ሀሳብ መግቢያ

4.1. ግማሽ እና ሩብ ክፍልፋዮችን ክለሳ 56
4.2 ሲሶዎች 58
4.3 የአንድ ሙሉ ነገር ክፍልፋዮች 59
የምዕራፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች 61

ምዕራፍ 5:- ሙሉ ቁጥሮች እስከ 1000

5.1. የ100 ብዜቶች 62
5.2. ሙሉ ቁጥሮች ከ101 - 1000 64
5.3 እስከ 1000 ያሉ የሙሉ ቁጥሮች የቁጥር ቤት ዋጋ 67
5.4 እስከ 1000 ያሉ የሙሉ ቁጥሮች ቅደም ተከተል 69
የምዕራፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች 72

ምዕራፍ 6:- ነጥቦች፣ ቀጥታ መስመሮች እና ቅርጾች (ምስሎች)

6.1 ማስመሪያን በመጠቀም ቀጥታ መስመሮችን መሣል 73
6.2 ጎነ አራት፣ ካሬ፣ ጎነ ሦስት እና ክብ ምስሎች 77
6.3 በአካባቢያችን የሚገኙ ምስሎች (ቅርጾች) 81
የምዕራፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች 82

ምዕራፍ 7:- ገንዘብ

7.1 ገንዘብን መደመርና መቀነስ 83
7.2 ግብይት 86
የምዕራፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች 89

ምዕራፍ 8:- ጊዜ

8.1 ሰዓትን በግማሽና በሩብ አቆጣጠር መቁጠር 90
8.2 ሰዓትና ደቂቃ 93
የምዕራፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች 95

ምዕራፍ 9:- መረጃ-አያያዝና-ድርድር


9.1 ቀላል መረጃዎችን መሰብሰብ 96
9.2. የቀላል መረጃ ሰንጠረዥ 97
9.3 የቁጥሮችና የቅርፃ ቅርጾች ቀላል ድርድር 99
የምዕራፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች 100

ምዕራፍ አንድ

እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ

1.1 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ክለሳ

ቀጥሎ ያሉትን ሣጥኖች ተመልከቱ። በእያንዳንዱ ሣጥን ውስጥ ያሉትን ምስሎች ብዛት በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ሙሉ።

		
_____ዶሮዎች	_____ተማሪዎች	_____ሙዞች

ተግባር 1.1 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን በመሆን ተወያዩባቸው።

1. አንድ ሰው ስንት አፍንጫ አለው?
2. ጓደኛችሁ ስንት ጆሮዎች አሉት/አላት?
3. በመማሪያ ክፍላችሁ ውስጥ ያሉት ጠረጴዛዎች ስንት ናቸው?
4. በመማሪያ ክፍላችሁ ውስጥ ያሉት ወንበሮች ስንት ናቸው?
5. በቀኝ እጆቻችሁ ላይ ስንት ጣቶች አሏችሁ?
6. በሁለቱ እጆቻችሁ ላይ ስንት ጣቶች አሏችሁ?
7. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

   ሀ) ከ1 ቀጥሎ ያለው ሙሉ ቁጥር _____ነው።

   ለ) ከ1 የሚቀድመው ሙሉ ቁጥር _____ነው።

   ሐ) የ9 ቀዳማይ ቁጥር _____ነው።

   መ) የ9 ተከታይ ሙሉ ቁጥር _____ ነው።

8. ቀጥለው ለተሰጡት ሙሉ ቁጥሮች ቀዳማይና ተከታይ ፈልጉ::

ሀ) የ10 ቀዳማይ _____ሲሆን ተከታይ _____ነው::

ለ) የ30 ቀዳማይ _____ሲሆን ተከታይ _____ ነው::


ሐ) የ51 ቀዳማይ _____ ሲሆን ተከታይ _____ ነው::

መ) የ75 ቀዳማይ _____ ሲሆን ተከታይ _____ነው::

ሠ) የ99 ቀዳማይ _____ሲሆን ተከታይ _____ነው::

መልመጃ-1 ሀ

1. ከሚከተለው ስዕል ምን ትረዳላችሁ?



2. ባዶ ቦታውን ሙሉ::

ሀ) 10 ፣ 15፣ 20፣ _____፣_____፣_____ ፣ _____፣45::

ለ) 10፣ 20፣ 30፣ _____፣_____፣_____ ፣ ____ ፣80::

ሐ) 5፣ 15፣ _____ ፣ _____፣ _____፣ _____::

3. የሚከተሉትን ቁጥሮች ስርአት ተገንዝባችሁ በስርአቱ መሰረት የቀሩትን ሙሉ ቁጥሮች በባዶ ቦታው ሙሉ::



ሀ) 5 _____፣ 15፣ _____፣ 25፣ _____ 35፣ 40፣ _____::

ለ) 18፣ 16፣ _____፣ _____፣ 10፣ _____፣ _____፣4::

ሐ) 78፣ 79፣ _____ ፣ _____፣ 82፣ _____፣ _____፣ _____::

መ) 99፣96፣ 93፣ _____፣ 87 _____፣ _____::

4. የሚከተለትን ጥንዶች በብዛታቸው < ፣>፣ = በመጠቀም አወዳድሩ::

ሀ.  ለ. 

ሐ. 

15 14

መ. 

40 37

ሠ. 15 _____10 + 5 ረ. 90 + 9 _____100

5. ለሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ቀዳማይ ሙሉ ቁጥሩን አግኙ::

ሀ) 16 ለ) 25 ሐ) 40 መ) 66 ሠ) 77 ረ) 84

6. ለሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ተከታይ ሙሉ ቁጥሩን አግኙ::

ሀ) 12 ለ) 23 ሐ) 37 መ) 55 ሠ) 89 ረ) 99

7. በተሰጡት ሁለት ቁጥሮች መካከል ያሉትን ሙሉ ቁጥሮች አንድ በአንድ በቅደም ተከተል ዘርዝሩ::

ሀ) 15 እና 22 ለ) 81 እና 95 ሐ) 65 እና 75 መ) 8 እና 17

8. ከተሰጡት ሙሉ ቁጥሮች ቀጥሎ ያሉትን አምስት አምስት ሙሉ ቁጥሮች በቅደም ተከተል ዘርዝሩ::

ሀ) 0 ለ) 10 ሐ) 2 መ) 40 ሠ) 5 ረ) 90

የቁጥር ቤት ፅንሰ ሀሳብ

ቀጥሎ የተመለከተው ሰንጠረዥ እስከ ሁለት የቁጥር ሆሄ ያላቸውን ሙሉ ቁጥሮች የቁጥር ቤትን ያመለክታል።

ቁጥር	የአስር ቤት	የአንድ ቤት	ሲነበብ
83	8	3	ሰማንያ ሶስት
49	4	9	አርባ ዘጠኝ
71	7	1	ሰባ አንድ

መልመጃ-1 ለ

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች በቁጥር ቤት ተንትኑ።

ምሳሌ:- 65 = 60 + 5 በዚህ ቁጥር ላይ 6 አስሮች እና 5 አንዶች አሉ።

ሀ) 88 = ___ + ___ በዚህ ቁጥር ላይ ___ አስሮች እና ___ አንዶች አሉ።
ለ) 62 = ___ + ___ በዚህ ቁጥር ላይ ___ አስሮች እና ___ አንዶች አሉ።
ሐ) 98 = ___ + ___ በዚህ ቁጥር ላይ ___ አስሮች እና ___ አንዶች አሉ።

2. ቀጥሎ ያሉትን ቁጥሮች በአሃዝ ፃፏቸው።

ሀ) 5 አስሮች እና 9 አንዶች = _____።
ለ) 8 አስሮች እና 5 አንዶች = _____።
ሐ) 4 አስሮች እና 0 አንዶች =_____።
መ) 6 አስሮች እና 6 አንዶች = _____።

3. የሚከተሉትን በአሃዝ ፃፏቸው።

ሀ) ሰማንያ ሶስት	መ) ሰባ አምስት	ሰ) አርባ አራት
ለ) አርባ ሰባት	ሠ) ሠላሳ ሁለት	ሸ) አስራ ሦስት
ሐ) ዘጠና ስድስት	ረ) ስልሳ ሦስት	ቀ) አስራ አምስት
		በ) አስራ ሰባት

4. በሚከተሉት ቁጥሮች ውስጥ የ4 ቁጥርን የቤት ዋጋ ሰይሙ።

ሀ) 84	ሐ) 74	ሠ) 94	ሰ) 43
ለ) 46	መ) 40	ረ) 48	ሸ) 99

1.2 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ ክለሳ

የቡድን ሥራ 1.1

1. ለሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች በምሳሌው መሠረት ድምራቸውን አግኙ::



8 + 7 = 15

2.



12 + 6 = 18

ሀ.




9 + 6 =

ለ.




12 + 7 =

ሐ.



15 + 5 =




5 + 8 = _____

3. ቀጥሎ የተሰጡትን ምስሎች በመመልከት በምሳሌው መሠረት ቀንሱ::



ሀ.





13 – 7 = 6

ለ.

18 – 13 = _____



ሐ.





20 – 10 = _____

መ.

15 – 8 = _____

4. ቀጥሎ የተመለከተውን የመደመር ሠንጠረዥ ሙሉ::

+	1	2	3	4	5	6	7	8	9	10
1	2		4							11
2		4		6						
3			6		8			11		13
4				8		10			13	
5					10		12			
6	7			10		12		14		
7		9					14		16	
8			11					16		18
9				13					18	
10		12			15					20

5. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስሉ።

ሀ. 8 – ☐ = 2

ለ. 4 + ☐ = 12

ሐ. 15 – ☐ = 4

6. የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች ፍቱ።

ሀ. አቶ አበበ 12 ብርቱካኖች ከጓሯቸው ለቅመው ለሶስቱ ልጆቻቸው ሁለት ሁለት ብርቱካን ሰጧቸው። አቶ አበበ ስንት ብርቱካኖች ይቀሯቸዋል?

ለ. አንድ ባለ ሁለት አሀዝ ቁጥር አስቡ። የአሰባችሁት ቁጥር የአንድ ቤት አሀዝ 7 ሆኖ በአስር ቤት እና በአንድ ቤት ያሉት ቁጥሮች ልዩነት 2 ቢሆን እናንተ ያሰባችሁት ቁጥር ስንት ነው?

ሐ. በክፍል ውስጥ 30 ተማሪዎች አሉ። 12ቱ ወንዶች ተማሪዎች ቢሆኑ የሴት ተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

መ. ሁለት ጓደኞቻችሁ አንዱ 3 ሌላው 5 ብርቱካኖች ቢሰጧችሁ አሁን በአጠቃላይ ስንት ብርቱካኖች አሏችሁ?

ተግባር 1.2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን በመሆን ተወያይባቸው።

1. የባለ አንድ አሀዝ ቁጥሮች ስንት ናቸው?
2. ትንሹ ባለ አንድ አሀዝ ቁጥር ስንት ነው?
3. ትልቁ ባለ አንድ አሀዝ ቁጥር ስንት ነው?
4. ትንሹ ባለ ሁለት አሀዝ ቁጥር ስንት ነው?
5. የትልቁ እና የትንሹ የባለ አንድ አሀዝ ቁጥር ልዩነት ስንት ነው?

1. የሚከተሉትን በምሳሌው መሠረት ደምሩ።


ምሳሌ፡- ✪✪✪✪✪✪✪✪✪✪ + ✪ = ✪✪✪✪✪✪✪✪✪✪✪

10 + 1 = 11

ሀ. /// /// + // =


10 + 2 =

ለ.



10 + 3 =

ሐ.



10 + 7 =

1.3 ባለአንድ አሃዝ ቁጥርን ከባለ ሁለት አሃዝ ቁጥር ጋር ያለ አለኻታና ያለ ብድር መደመርና መቀነስ

1. የሚከተሉትን ደምሩ::

ሀ. 10 + 1 = _____ መ. 10 + 4 =_____ ሰ. 10 + 7 = _____





ለ. 10 + 2 = _____ ሠ. 10 + 5 =_____ ሸ. 10 + 8 = _____

ሐ. 10 + 3 = _____ ረ. 10 + 6 =_____ ቀ. 10 + 9 = _____

2. የሚከተሉትን በምሳሌው መሰረት ቀንሱ::

ምሳሌ:-

		
10 – 1 = 9		
ሀ. 		
10 – 2 = _____		
ለ. 		
10 – 8 = _____		

ሐ.			
	60	– 10	= _____
መ.			
	59	– 2	= _____
ሠ.			
	58	– 8	= _____

3. ባዶ ቦታውን ሙሉ::

ሀ. 57 - 4 = ☐	ሠ. 65 - 4 = ☐	ቀ. 88 - 8 = ☐
ለ. 47 - 3 = ☐	ረ. 68 - 8 = ☐	በ. 98 - 8 = ☐
መ. 56 - 6 = ☐	ሸ. 78 - 8 = ☐	ተ. 99 - 9 = ☐

መልመጃ-1 ሐ

1. በቤታችሁ ውስጥ 15 በጎች አሉ:: ሶስቱ በጎች ተሸጡ:: በቤት ውስጥ የቀሩት በጎች ስንት ናቸው?
2. አቶ አለማየሁ በኪሱ 18 ብር አለው:: ለአቶ ክንፈ 7 ብር ቢሰጠው አለማየሁ በኪሱ የቀረው ብር ምን ያህል ነው?
3. አንድ ተማሪ ከአባቱ 10 ብር ከእናቱ 6 ብር ለደብተርና እስክሪብቶ መግዣ ተሰጠው:: በአጠቃላይ ተማሪው ከቤተሰቡ ስንት ብር ተሰጠው?
4. የ6፣ 7 እና 4 ድምር ስንት ነው?

1.4 ባለአንድ አሃዝ ቁጥርን ከባለ ሁለት አሃዝ ቁጥር በአለኽታ እና በብድር መደመርና መቀነስ

ምሳሌ፦ ሀ.

አሃዝ	አስር ቤት	የአንድ ቤት
36 +5 41	□□□□□□□□□□ □□□□□□□□□□ □□□□□□□□□□	□□□ □□□
	30 +	6
	———————	□□□□□ 5
41	□□□□□□□□□□ □□□□□□□□□□ □□□□□□□□□□ □□□□□□□□□□	□
	40 + 1 = 41	

ምሳሌ፦ ለ. 62 - 7

60 + 2 – 7

50 + 12 – 7

አሃዝ	አስር ቤት	አንድ ቤት
62	6	2
–7	–	7
55	□□□□□□□□□□ □□□□□□□□□□ □□□□□□□□□□ □□□□□□□□□□ □□□□□□□□□□ 50	⁄⁄⁄⁄⁄⁄ ⁄□□□□□ 12
	–	⁄⁄⁄⁄⁄⁄⁄ 7
	50	□□□□□ 5
		55

ተግባር 1.3 በቡድን በመሆን አስሉ።

አስሉ

ሀ. 72 +8 ——— ——— ለ. 68 +2 ——— ——— ሐ. 42 +8 ——— ——— መ. 87 +3 ——— ———

አስሉ

ሀ. 63 – 8 = 55 ለ. 24 – 6 = ____ ሐ. 31 – 9 = ____ መ. 45 – 8 = ____

☺ **አስተውሉ**

የመደመርን ውጤት በመቀነስ የመቀነስን ውጤት በመደመር ማረጋገጥ ትችላላችሁ።

ምሳሌ፦

ሀ) 63 + 4 = 67 ምክንያቱም 67 – 4 = 63 ስለሆነ ነው።

ለ) 83 + 9 = 92 ምክንያቱም 92 – 9 = 83 ስለሆነ ነው።

ሐ) 72 –10 = 62 ምክንያቱም 62 + 10 = 72 ስለሆነ ነው።

መ) □ + 54 = 92 ምክንያቱም 92 – 54 = □ ስለሆነ ነው።

ሠ) □ - 3 = 70 ምክንያቱም 70 + 3 = □ ስለሆነ ነው።

መልመጃ-1 መ

1. የቃላት ፕሮብሌሞች (ጥያቄዎች) ፍቱ።

ሀ) አጥናፉ ከቤት ወደ ት/ቤት ለመሄድ 7 ኪ.ሜ ይጓዛል። በደርሶ መልስ ጉዞ አጥናፉ ምን ያህል ኪ.ሜ. ይጓዛል።


ለ) በአንድ የእግር ኳስ ጨዋታ ሁለት ቡድኖች ይጫወታሉ። በእያንዳንዱ ቡድን 11 ተጫዋቾች ይሰለፋሉ። በአጠቃላይ በሜዳው ላይ ያሉ ተጫዋቾች ስንት ናቸው?

1.5 ሁለት ባለ ሁለት አሃዝ ሙሉ ቁጥሮችን ያለ አለኝታ እና ያለ ብድር መደመር እና መቀነስ

መቀነስ


ቀጥለው የተሰጡትን ምስሎች በመመልከት ቀንሱ።

ሀ)



18 — 12 = _____

ለ)



24 — 12 = _____

ሐ)



60 — 20 = _____

መ)



13 — 8 = _____

አስሉ

ሀ) 87 - 74 _____	ሐ) 75 - 34 _____	ሠ) 64 -10 _____	ሰ) 23 -11 _____
ለ) 54 - 21 _____	መ) 90 - 40 _____	ረ) 99 - 81 _____	ሸ) 88 - 25 _____

መቀነስ

ለምሳሌ፡-

ሀ) 80
-20
60



80 - 20 = 60

መልመጃ-1 ሠ

1. የሚከተሉትን ድምሮች ፈልጉ::
   - ሀ) 23 + 34 = _____
   - ሐ) 70 + 30 = _____
   - ለ) 61 + 36 = _____
   - መ) 61 + 37 = _____
2. የሚከተሉትን በአሃዝ ፃፉ::
   - ሀ) ዘጠኝ አስሮች እና ሁለት አንዶች::
   - ለ) አንድ አስር እና ሰባት አንዶች::
   - ሐ) አምስት አንዶች እና ስድስት አስሮች::
   - መ) ስምንት አስሮች እና ስምንት አንዶች::
   - ሠ) ስድስት አስሮች እና ስምንት አንዶች::
   - ረ) ሁለት አስሮች እና ሁለት አንዶች::
3. የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች ፍቱ::
   - ሀ) እኔ አንድ ቁጥር አሰብኩ:: ከቁጥሩ ላይ አምስት ሲቀነስ ውጤቱ 32 ይሆናል:: እኔ ያሰብኩት ቁጥር ስንት ነበር?
   - ለ) በአንድ ክፍል ውስጥ 30 ተማሪዎች አሉ:: የወንዶቹ ተማሪዎች ቁጥር ከሴት ተማሪዎች ቁጥር በ 4 ይበልጣል:: በክፍሉ ውስጥ ስንት ወንዶች እና ሴት ተማሪዎች አሉ?
   - ሐ) ወ/ሮ በላይነሽ ከአንድ ሱቅ 8 ብርቱካኖች እና ከሌላ ሱቅ ደግሞ 3 ብርቱካኖች ገዙ:: በአጠቃላይ ከሁለቱ ሱቆች ስንት ብርቱካኖች ገዙ?
   - መ) የሁለት ተከታታይ ሙሉ ቁጥሮች ድምር 41 ነው:: ቁጥሮቹ እነማን ናቸው?
4. በመጽሐፍት መደርደሪያ ላይ 5 የሂሳብ፣ 8 የአካባቢ ሳይንስ እና 10 የእንግሊዝኛ መጽሐፎች አሉ::
   - ሀ. በመደርደሪያው ላይ ያሉት መጽሐፍት ብዛት ስንት ነው?
   - ለ. የእንግሊዘኛ መጽሐፍት ብዛት ከሂሳብ መጽሐፍት ብዛት በስንት ይበልጣል?

1.6 ሁለት ባለ ሁለት አሃዝ ሙሉ ቁጥሮችን በአለኻታ እና በብድር መደመር እና መቀነስ

ምሳሌ፡- ሀ. 15 + 28

አሃዝ	የአስር ቤት	የአንድ ቤት
15 + 28 = 43	1 + 2 3 + 1	5 + 8 13 = 10 + 3
_____	4	3

ለ. 68
- 29
39

አሃዝ	የአስር ቤት	የአንድ ቤት
60 + 8 20 + 9	60 20	8 9

የአስር ቤት	የአንድ ቤት
50	18
- 20	9
30	9
30 + 9 = 39	

ተግባር 1.4

1. የሚከተሉትን አስሉ::

ሀ) 68 + 57 = _____

ለ) 78 − 29 = _____

ሐ) 18 + 66 = _____

መ) 64 − 29 = _____

ሠ) 73 + 88 = _____

ረ) 18 − 9 = _____

ሰ) 99 + 11 = _____

ሸ) 38 − 29 = _____

2. የእኔ እድሜ ከወንድሜ እድሜ በ4 ዓመት ያንሳል:: የወንድሜ እድሜ አሁን 12 ዓመት ነው:: የእኔ እድሜ አሁን ስንት ነው?

3. ሰለሞን 3 መፅሐፎችን በ45 ብር ገዛ:: ሜሮን 2 ደብተሮችን በ 7 ብር ገዛች:: በጠቅላላው ሁለቱ ልጆች ስንት ብር ከፈሉ?

4. የሳጥኑን ዋጋ ፈልጉ::

ሀ) 18 − 7 = □ ሐ) 76 + 80 = □ ሠ) 49 − □ = 25

ለ) 36 + □ = 45 መ) 68 + □ = 93 ረ) □ + 55 = 80

በአለኻታ የመደመር ስሌቶችን ውጤት ፈልጉ::

ለምሳሌ፡-

ሀ.

የ10 ቤት	የ1ቤት
1	5
+ 2	8
4	3

የአንድ ቤቶችን ድምር 5+8 = 13 ነገር ግን 13 = 10+3 እዚህ ላይ 10 ማለት 1 አስር ማለት ነው:: ስለዚህ 3 ፅፈህ/ሽ 1ን ወደ አስር ቤት ውሰደው/ውሰጅው ይህም 1 + 1 + 2 = 4 አስሮች ማለት ነው::

ለ. 68
−29
39

አንዶችን እና አስሮችን በቅደም ተከተል ቀንስ/ሽ። ከ8 አንዶች 9 አንዶችን መቀነስ አይቻልም። ስለዚህ ከ6 አስሮች ላይ 1 አስር (ወይም 10 አንዶች) በመበደር።
8 አንዶች እና 10 አንዶች 18 አንዶች ይሆናል። ከ18 አንዶች 9 አንዶችን ሲቀነስ 9 አንዶች ይቀራል።
በመቀጠል ከ5 አስሮች ላይ 2 አስሮች መቀነስ
(5 – 2 = 3)። ስለዚህ 68 – 29 = 39

መልመጃ-1 ረ

1. ድምሩን አግኙ

ሀ.	25	ለ.	44	ሐ.	69
	+ 37		+ 26		+ 26
መ.	77	ሠ.	19	ሠ.	86
	+ 23		+ 74		+ 13

2. ልዩነቱን አግኙ

ሀ.	78	ለ.	86	ሐ.	97
	− 39		− 38		+ 48
መ.	95	ረ.	90	ሸ.	80
	− 59		− 35		− 56

1.7 በመደመር እና በመቀነስ እስከ 100 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች የሚሰሩ የቃላት ፕሮብሌሞች

ተግባር 1.5

1. አለም ትላንት 16 ዶሮዎችን፣ ዛሬ ደግሞ 11 ዶሮዎችን ሸጠች። በአጠቃላይ አለም ስንት ዶሮዎችን ሸጠች?
2. ተሰማ በዘንድሮ የምርት ዘመን 10 ኩንታል ጤፍ፣ 16 ኩንታል ስንዴ እና 15 ኩንታል በቆሎ አመረተ። በአጠቃላይ በምርት ዘመኑ ምን ያህል ኩንታል እህል አመረተ?
3. አንድ ተማሪ ከመኖርያ ቤቱ እስከ ት/ቤቱ ድረስ 10 ኪ.ሜ ተጓዘ። ተማሪው በደርሶ መልስ ምን ያህል ኪ.ሜ ተጓዘ?
4. የስድስት አሥሮች፣ የሁለት አንዶች እና የሶስት አስሮች፣ የአራት አንዶች ጠቅላላ ድምር ስንት ነው?

የምዕራፍ የማጠቃለያ መልመጃዎች

ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ::

1. ኤልሳ 3 ደብተሮችን እያንዳንዳቸውን በ 5 ብር ሒሣብ ገዛች:: ኤልሳ በጠቅላላው ስንት ብር ከፈለች?
   ሀ. 35 ለ. 53 ሐ. 15 መ.5
2. ዓለሙ ጧት ጧት 100 ሜትር ርቀት ይሮጣል:: ይህንን ርቀት በ20 ደቂቃ ይጨርሳል:: ዓለሙ በእያንዳንዱ ደቂቃ ስንት ሜትር ይሮጣል?
   ሀ. 5 ሜ ለ. 10ሜ ሐ. 20ሜ መ. 25ሜ
3. አንድ ሙሉ ቁጥር አሰብኩ:: ከአሰብኩት ቁጥር ላይ 10 ስደምርበት ውጤቱ 15 ሆነ:: ያሰብኩት ቁጥር ስንት ነበር?
   ሀ. 5 ለ. 4 ሐ. 3 መ. 2
4. የ16 የቀዳሚ ቀዳሚ ቁጥር ስንት ነው?
   ሀ. 15 ለ. 14 ሐ. 13 መ. 17
5. የ16 የተከታይ ተከታይ ቁጥር ስንት ነው?
   ሀ. 17 ለ. 18 ሐ. 19 መ. 15
6. የተሰጡትን ሙሉ ቁጥሮች በመተንተን ባዶ ቦታውን ሙሉ::

   ለምሳሌ:- 75 = 70 + 5

   ሀ. 65 = _____ + 5_____ መ. 99 = _____ + 9
   ለ. 78 = _____ + _____ ሠ. 100 = _____ + 10
   ሐ. 87 = 80 + _____
7. የሚከተሉትን አስሉ::
   ሀ. ከሰባት አስሮች ላይ ሦስት አስሮችን ብትቀንሱ ልዩነቱ ስንት ይሆናል?
   ለ. ዘጠኝ አስሮችና ስምንት አንዶች በአሀዝ ሲገለጽ _____ ነው::
   ሐ. የአስራ አራት እጥፍ ስንት ነው?
8. የአንድ ሒሳብ መፅሐፍ ዋጋ 20 ብር ቢሆን የሦስት ተመሳሳይ መፅሐፍት ዋጋ ስንት ብር ይሆናል?
9. ብርሀኑ 45 እንቁላል ጣይ ዶሮዎች እና 15 በጐች ገዝቶ ያረባል:: ብርሃኑ በድምሩ ስንት የቤት እንስሳት አሉት?
10. ቀንሱ ሀ. 87 ለ. 98 ሐ. 92
    - 19 - 79 - 64
    ☐ ☐ ☐
11. ድምሩን አግኙ::

    ሀ. 47 ለ. 56 ሐ. 87
    + 25 + 43 + 12
    ☐ ☐ ☐
12. በ0 እና በ100 መካከል የሚገኙ ሙሉ ቁጥሮችን በአስር በአስር ርቀት በሠንጠረዥ አስቀምጡ::

ምዕራፍ ሁለት

ማባዛትና ማካፈል እስከ 100

2.1. ያለ ቀሪ በ2 እና በ10 ማባዛትና ማካፈል ክለሳ

2.1.1 በ2 ማባዛት እና ማካፈል

በ2 ማባዛት

ተግባር 2.1

በእያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ የሚገኙትን ጠጠሮች በመቁጠር የማባዛት ውጤቱን ባዶ ቦታው ላይ ሙሉ::

1.  1 × 2 = _____
   2

2.  = 2 × 2 = _____
   2 2

3.  = 3 × 2= _____
   2 2 2

4.  = 4 × 2= _____
   2 2 2 2


5.  = 5 × 2= _____
   2 2 2 2 2

6.  = 6 × 2= ___
   2 2 2 2 2 2

ምሳሌ፡-



6 + 6 = 2 × 6 = 12



2 + 2 + 2 + 2 + 2 + 2 = 6 × 2 = 12

በሒሳባዊ አረፍተ ነገር ሲገለፅ 6 × 2 = 12፣ ሲነበብ 6 ሲባዛ በ2 እኩል ይሆናል 12 ወይም 6 ጊዜ 2 ይሆናል 12 ተብሎ ነው::

2 × 6 = 12

2 እና 6 የ12 **አብዥዎች** ሲባሉ 12 ደግሞ የ2 እና የ6 **ብዜት** ይባላል::

የሁለት ብዜትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ::

×	0	1	2	3	4	5	6	7	8	9	10	11	12	13	14	15	16	17	18	19	20
2	0	2	4	6	8	10	12	14	16	18	20	22	24	26	28	30	32	34	36	38	40

☺ አስተውሉ


በሁለት ማባዛት ማለት ውጤቱ የሙሉ ቁጥሩን እጥፍ አደረግን ማለት ነው።

ሀ. 2 × 0 = 0	ሠ. 2 × 4 = 8	በ. 3 × 2 = 6
ለ. 2 × 1 = 2	ረ. 2 × 5 = 10	ተ. 4 × 2 = 8
ሐ. 2 × 2 = 4	ሰ. 0 × 2 = 0	ቸ. 5 × 2 = 10
መ. 2 × 3 = 6	ሸ. 1 × 2 = 2	

መልመጃ-2 ሀ

1. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች ሙሉ።

ሀ.




_____+_____=_____ ወይም 2 × ____ = _____

ለ.



_____ + 9 = 18 ወይም _____ × _____ = 18

ሐ.



አንዷ ቦታ ካሬ ትባላለች

አንድ ካሬ አንድ እንቁላል ታስቀምጣለች። በጠቅላላው ስንት እንቁላሎችን ማስቀመጥ ይቻላል? በማባዛት ስሌት ስናስቀምጠው _____×_____=_____

2. ሳጥኑን የሚወክሉ ሙሉ ቁጥሮች ፈልጉ::

ሀ. ☐ × 2 = 18 ሐ. 2 × ☐ = 42

ለ. ☐ × 2 = 24 መ. 2 × ☐ = 46

3. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች መካከል የ2 ብዜት የሆኑትን ሙሉ ቁጥሮች በማክበብ ለዩ::

ሀ. 42፣45፣24፣6፣7፣69፣75፣82፣94፣99፣3

ለ. 5፣7፣9፣10፣12፣13፣16፣20፣23፣27፣30

ሐ. 15፣19፣21፣26፣3፣34፣37፣39፣48፣50፣55

መ. 52፣56፣59፣62፣63፣66፣71፣73፣76፣77፣85

4. በ 31 እና በ41 መካከል የሚገኙ የሁለት ብዜቶች ስንት ናቸው? በቅደም ተከተል ዘርዝሩ::


5. አንድ የዶሮ እርባታ ጣቢያ 47 እንቁላል ጣይ ዶሮዎች አሉት:: የዶሮዎቹ እግር በጠቅላላው ስንት ነው?

6. በክፍል ውስጥ 36 ወንበሮች አሉ:: በእያንዳንዱ ወንበሮች ላይ ሁለት ሁለት ተማሪዎች ተቀምጠው ይገኛሉ:: በክፍሉ ውስጥ ያሉት ተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

7. አንድ ወላጅ አባት 42 ደብተሮች ገዛ:: እያንዳንዱን ደብተር በ 2 ብር ዋጋ ቢገዛ በጠቅላላው ደብተሮችን በስንት ብር ገዛ?

በሁለት ማካፈል (በ2 ማካፈል)

ሀ.



8 ÷ 2 = 4

	÷ 2
2	1
4	2
6	3
8	4

8 ÷ 2 = 4

8 ተካፍይ

2 አካፍይ

4 ድርሻ ይባላል።

መልመጃ-2 ለ

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ።

ሀ. 26 ÷ 2 = ☐ መ. 16 ÷ 2 = ☐ ረ. 44 ÷ 2 = ☐

ለ. 30 ÷ 2 = ☐ ሠ. 40 ÷ 2 = ☐ ሸ. 50 ÷ 2 = ☐

2. ሠንጠረዦቹን በደብተራችሁ ላይ ገልብጡና ባዶ ቦታውን ሙሉ።

ሀ.

	÷ 2
36	
38	
46	
	24
62	
	7

ለ.

	÷ 2
20	
30	
40	20
50	
60	

በምሳሌው መሠረት በሣጥኑ ውስጥ የሚገባውን የቁጥር ዋጋ አግኙ።

ምሳሌ 1፦ 16 ÷ 2 = 8

ምክንያቱም 8 × 2 = 16

ምሳሌ 2፦ 22 ÷ 2 = 11 ምክንያቱም 2 × 11 = 22

ምሳሌ 3፦ 1) 16 ÷ 2

የአንድ ቤት ድርሻ

5 + 3

የአስር ቤት ድርሻ

$2\overline{)10 + 6} = 2\overline{)10}^{5} + 2\overline{)6}^{3} = 8$

መልመጃ-2 ሐ

1. በምሳሌው መሠረት በሣጥኑ ውስጥ የሚገባውን የቁጥር ዋጋ አግኙ::

ሀ. $20 \div 2 = \square$ ሐ. $40 \div \square = 20$

ለ. $18 \div 2 = \square$ መ. $82 \div \square = 41$

2. የሚከተሉትን በምሳሌው መሠረት አስሉ::

ሀ. $52 \div 2 = \dfrac{25 + 1}{2 \overline{)\, 50 + 2}} = \dfrac{25}{2 \overline{)\, 50}} + \dfrac{1}{2 \overline{)\, 2}} = 26$

ለ. $66 \div 2 = \dfrac{\square\,\square}{2 \overline{)\, 60 + \square}} = \dfrac{\square}{2 \overline{)\, 60}} + \dfrac{\square}{2 \overline{)\, 6}} = \square$

ሐ. $84 \div 2 = \dfrac{\square + \square}{2 \overline{)\, 80 + 4}} = \dfrac{\square}{2 \overline{)\, 80}} + \dfrac{\square}{2 \overline{)\, 4}} = \square$

3. አቶ ሀሰን 24 ደብተሮችን ገዝቶ ለሁለት ልጆቹ እኩል ቢያካፍላቸው እያንዳንዳቸው ስንት ደብተሮች ይደርሳቸዋል?

4. የአስቻለው እድሜ 40 ዓመት ነው:: አስቻለው የእህቱን የአለሚቱን እድሜ እጥፍ ቢሆን የአለሚቱ እድሜ ስንት ነው?


2.1.2. በ10 ማባዛትና ማካፈል


በ10 ማባዛት

ተግባር 2.2 በቡድን በቡድን በመሆን ተወያዩበት::


ሳጥኑን ሙሉ::

ምሳሌ:-

1.  $1 \times 10 = \boxed{10}$


2. 

$2 \times 10 = \boxed{20}$

3. 


10 + 10 + 10

$3 \times 10 = \square$

4. 

10 + 10 + 10 + 10

$4 \times 10 = \square$

5. 

10 + 10 + 10 + 10 + 10

$5 \times 10 = \square$

የ10 ብዜት

$1 \times 10 = 10$	$4 \times 10 = 40$	$7 \times 10 = 70$	$10 \times 10 = 100$
$2 \times 10 = 20$	$5 \times 10 = 50$	$8 \times 10 = 80$	
$3 \times 10 = 30$	$6 \times 10 = 60$	$9 \times 10 = 90$	

መልመጃ-2 መ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በሣጥኑ የሚገባውን ቁጥር ፈልጉ::

ሀ. $\square \times 10 = 60$ ሐ. $\square \times 10 = 10$

ለ. $10 \times \square = 80$ መ. $10 \times \square = 30$

2. ሠንጠረዡን በደብተራችሁ ገልብጡና ባዶ ቦታውን ሙሉ::

ሀ.

×	5	7	8	2	9	10
10						

ለ.

×	3	4	5	6	7	8	10
10						80	

የ10 ብዜቶች ዘርዝሩ::

ለ. በዜሮ እና በ99 መካከል የሚገኙትን የ10 ብዜቶች ዘርዝሩ::

ሐ. የ6ን እና የ5ን 10 እጥፍ ፈልጉ::

በ10 ማካፈል

ተግባር 2.3 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ መልስ ስጡ::

1. 30 ሙዞችን ለ10 ተማሪዎች ብናከፋፍላቸው ለእያንዳንዳቸው ስንት ስንት ሙዞች ይደርሳቸዋል? ስናካፍል በእጃችን የሚቀር ሙዝ ይኖራል?
2. በክፍላችሁ ውስጥ የሚገኙትን 40 ወንበሮች በአስር በአስር ብትመድቧቸው ስንት ምድብ ታገኛላችሁ?
3. በ10 እና በመቶ መካከል የሚገኙት ቁጥሮች ሁሉ ለ10 ያለ ቀሪ ሊካፈሉ ይችላሉን?

ምሳሌ 1:-



20 ሻማዎች

$20 \div 10 = 2$ ምክንያቱም $2 \times 10 = 20$ ስለሆነ

ምሳሌ 2:- $40 \div 10 = 4$ ምክንያቱም $4 \times 10 = 40$ ስለሆነ

መልመጃ-2 ሠ

1. የሚከተሉትን አስሉ::

ሀ. $50 \div 10 = \square$ ሐ. $100 \div 10 = \square$

ለ. $70 \div 10 = \square$ መ. $90 \div 10 = \square$

2. ሣጥኑን የሚተኩትን ሙሉ ቁጥሮች ፈልጉ::

ሀ. □ ÷ 10 = 2 ሐ. 40 ÷ □ = 4

ለ. □ ÷ 10 = 7 መ. 20 ÷ □ = 2

3. በሠንጠረዡ ውስጥ ባዶ ቦታውን ሙሉ::

ሀ.

	÷ 10
10	
20	
40	
	6
80	
100	

2.2. በ0 እና በ1 ማባዛት እና ለ1 ማካፈል

2.2.1. በ0 ማባዛት

ተግባር 2.4 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ መልስ ስጡ::

1. ዜሮ በማባዛት ያለው ልዩ ባህርይ ምንድነው? ተወያዩ::
2. ዜሮን ከሌሎች ሙሉ ቁጥሮች ጋር ማባዛት ይቻላልን?
3. ዜሮ ስንል በቁሳቁስ ብዛት ልንገልፀው እንችላለን?
4. ማንኛውም ሙሉ ቁጥር በዜሮ ሲባዛ ውጤቱ ምን ይሆናል?

ምሳሌ:-

1. 0 + 0 + 0 = 0 × 3 = 0
2. 0 + 0 + 0 + 0 + 0 = 0 × 5 = 0
3. 0 + 0 = 0 × 2 = 0
4. ሀ. 1 × 0 = 0 × 1 = 0

   ለ. 2 × 0 = 0 × 2 = 0

   . .

   . .

   . .

   99 × 0 = 0 × 99 = 0

መልመጃ-2 ረ

1. የሚከተሉትን የዜሮን ባህርይ በማስታወስ አስሉ::

ሀ. $60 \times 0 = \square$ ሐ. $8 \times 0 = \square$ ሠ. $100 \times 0 = \square$

ለ. $7 \times 0 = \square$ መ. $0 \times 0 = \square$

2.2.2. በ1 ማባዛትና ለ1 ማካፈል

ተግባር 2.5

1. ሙሉ ቁጥሮች በ1 ሲባዙ ውጤቱ (ብዜቱ) ምን ሊሆን ይችላል? ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ::
2. ሙሉ ቁጥሮች በ1 ቢካፈሉ ድርሻው (ውጤቱ) ምን ሊሆን ይችላል? ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ::
3. ማንኛውም ሙሉ ቁጥር በ1 ማብዛትም ሆነ ማካፈል ሙሉ ቁጥሩን ይቀይረዋል ወይስ አይቀይረውም? በቡድን ተወያዩበት::

ምሳሌ:-

1.  $2 \times 1 = 2$

$1 + 1 = 2$


2.  $1 \times 2 = 2$

3.  $1 \times 3 = 3$

4.  $3 \times 1 = 3$

$1 + 1 + 1 = 3$

ለ1 ማካፈል

ምሳሌ 1:- 

$2 \div 1 = 2$

ምሳሌ 2፦ 

1 × 3 = 3

3 ÷ 1 = 3

መልመጃ-2 ሸ

1. የሚከተሉትን አስሉ::

ሀ. 1 × 5 = _____ ሐ. (0+3) × 1 = _____ ሠ. (30 + 0) × 1 = _____


ለ. 5 × 1 = _____ መ. (2+4) × 1 = _____ ረ. 1 × (0 + 30) = _____

2.3. ማባዛትና ማካፈል በ3፣ በ4፣ በ5፣ በ6፣ በ7፣ በ8 እና በ9

2.3.1. በ3 ማባዛትና ማካፈል


ተግባር 2.6

1. የ3 ብዜት የሆኑትን ሙሉ ቁጥሮች መዘርዘር ትችላላችሁ?
2. በ1 እና በ10 መካከል የ3 ብዜት የሆኑ ስንት ሙሉ ቁጥሮች አሉ?
3. 13 የ3 ብዜት ነውን?

ምሳሌ፦ 

1 × 3 = 3


1 ምድብ 3 ብርቱካኖች ያለው::



2 × 3 = 6

3 + 3 = 6

2 ምድቦች እያንዳንዳቸው 3 ብርቱካኖች አሏቸው::




3 + 3 + 3 = 9


3 ምድቦች እያንዳንዳቸው 3 ብርቱካኖች አሏቸው::

ስለዚህ 3 × 3 = 9

ምሳሌ:-

1. 

$3 \times 1 = 3$

2. 

$3 \times 6 = 18$

መልመጃ-2 ቀ


1. የሚከተሉትን ምስሎች በመገንዘብ ባዶ ቦታውን ሙሉ::

ሀ. 


$\square \times 3 = \square$

ሐ. 


$\square \times 3 = \square$

ለ. 


$\square \times 3 = \square$

መ. 

$\square \times 3 = \square$

ሠ. 

$\square \times 3 = \square$

ረ. 

$\square \times 3 = \square$

2. በሣጥኖች የሚገቡትን ሙሉ ቁጥሮች ፈልጉ::

ሀ. $\square \times 3 = 21$ ሐ. $3 \times \square = 36$


ለ. $\square \times 3 = 24$ መ. $3 \times \square = 39$

በ3 ማካፈል


ተግባር 2.7

1. ሁሉም የ3 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች ለ3 ይካፈላሉን?
2. በ10 እና በ40 መካከል የሚገኙትን የ3 ብዜቶች ዘርዝሩ::
3. ከ 0 በመጀመር ሦስት ሦስት እየደመራችሁ እስከ 42 ድረስ የሚገኙትን ቁጥሮች ፃፉ::

ምሳሌ:-



15 ÷ 3 = 5




15 ዳኪዬች በ3 ምድቦች ቢመደቡ እያንዳንዱ ምድብ አምስት ዳኪዬዎች ይኖሩታል::

መልመጃ-2 በ


1. በምሳሌው መሠረት ባዶ ሳጥኑን ሙሉ::

ሀ.






ለ.




18 ÷ 3 = ☐




☐ ÷ 3 = ☐

ሐ.



መ.



ሠ.

ሀ	1	2	4	7	9	12	15	17	21	23	30
ሀ × 3	3	6									

ረ.

ሀ	3	6	9	12	15	18	21	24	30	33	36	39	42
ሀ ÷ 3	1	2	3										

2. የሚከተሉትን በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ያልተሟሉትን ሙሉ ቁጥሮች አሟሉ።

ሀ.

1	2	3	4	5	6	7	8	9	10
11		13		15		17		19	
21		23		25		27		29	
31		33		35		37		39	
41		43		45		47		49	50
	52		54		56		58		60
	62		64		66		68		70
	72		74		76		78		80
	82		84		86		88		90
91		93		95		97		99	

ለ. በአንድ እና በመቶ መካከል ስንት የ3 ብዜቶች አሉ?

ሐ. ሁሉም የ3 ብዜቶች ለ3 ይካፈላሉ? አዎን ከሆነ እንዴት? አብራሩ።

2.3.2 በ4 እና በ5 ማባዛትና ማካፈል

ተግባር 2.8

1. የ4 ብዜቶች ሁሉ የ5 ብዜት ሊሆኑ ይችላሉን? ተወያዩባቸው።
2. በ1 እና በ20 መካከል የሚገኙ የ4 እና የ5 ብዜቶችን ዘርዝራችሁ ያላቸውን ግንኙነት ተወያዩበት።
3. በ1 እና በ20 መካከል የሚገኙት የ4 እና የ5 ብዜቶች እኩል ናቸውን?

ሀ. በአራት ማባዛት

ምሳሌውን ተመልከቱ።

1.  $1 \times 4 = 4$

2.  $2 \times 4 = 8$

3.  $3 \times 4 = 12$

ለ. በአምስት ማባዛት

1.  $1 \times 5 = 5$

2.  $2 \times 5 = 10$

3.  $3 \times 5 = 15$


መልመጃ-2 ተ

1. ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዶ ቦታውን ሙሉ።



4 × 2 = _____

ለ.



4 × _____ = ☐

ሐ.




5 × 4 = ☐

በ4 ማካፈል

ምሳሌ፡-


1)



8 ÷ 4 = 2


ምክንያቱም 2 × 4 = 8 ስለሆነ

2)



16 ÷ 4 = 4

ምክንያቱም 4 × 4 = 16 ስለሆነ

3) 

$$40 \div 4 = 10$$

ምክንያቱም $10 \times 4 = 40$ ስለሆነ

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምሳሌው መሠረት አስሉ::

ምሳሌ:-

1) $20 \div 4 = 5$ ምክንያቱም $5 \times 4 = 20$ ስለሆነ

ሀ. $4 \div 4 =$ _____ ሐ. $5 \div 5 =$ _____

ለ. $12 \div 4 =$ _____ መ. $20 \div 5 =$ _____

3. የሳጥኑን ቦታ ሙሉ::

ሀ. 40፣☐፣ 32፣☐፣☐፣20፣☐፣☐፣☐፣4::

ለ. 50፣45፣☐፣☐፣30፣25፣☐፣15፣10፣☐::

4. ሳጥኑን የሚተካውን ሙሉ ቁጥር አግኙ::

ሀ. ☐ × 4 = 8 ፣ 8 ÷ ☐ = 4 መ. ☐ × 5 = 10፣10 ÷ ☐ = 5

ለ. ☐ × 4 = 16 ፣16 ÷ ☐ = 4 ሠ. ☐ × 5 = 15፣ 15 ÷ ☐ = 5

ሐ. 4 × ☐ = 28 ፣ 28 ÷ ☐ = 7 ረ. ☐ × 5 = 25፣ 25 ÷ ☐ = 5

5. በቀለ 10 የማንጎ ችግኝ መደብ አዘጋጅቷል:: በእያንዳንዱ መደብ አራት አራት ችግኞችን ቢተክል በቀለ ስንት የማንጎ ችግኞች ይኖሩታል?

6. በአንድ ክፍል ውስጥ 45 ተማሪዎች አሉ:: መምህራቸው በእያንዳንዱ ቡድን አምስት ተማሪዎች አስቀምጠው እንዲወያዩ ቢያደርጉ ስንት ቡድኖች ተፈጠሩ?

7. እስማኤል 10 ግመሎች አሉት:: የእስማኤል ግመሎች እግር በጠቅላላው ስንት ነው?

8. በ23 እና በ45 መካከል የሚገኙ የ4 ብዜቶችን ዘርዝሩ::

9. አንድ ጤና ጣቢያ ባለፈው ሳምንት 14 የኤድስ ህሙማንን መዘገበ:: በዚህ ሳምንት ውስጥ ደግሞ በአምስት እጥፍ ጨመረ:: በአጠቃላይ በዚህ ሣምንት ስንት የኤድስ ሕሙማን ተመዘገቡ?

2.3.3 በ6፣ 7፣ 8 እና 9 ማባዛትና ማካፈል

በ6 ማባዛትና ማካፈል


ተግባር 2.9

1. ሁሉም የ6 ብዜቶች የ3 ብዜት ውጤቶች መሆን ይችላሉን?
2. ሁሉም ለ3 ሊካፈሉ የሚችሉ ሙሉ ቁጥሮች ለ6 ሊካፈሉ ይችላሉን? ወይስ በከፊል? ተወያዩባቸው::

ምሳሌ፦-



$1 \times 6 = 6$




$2 \times 6 = 12$




$3 \times 6 = 18$

ምሳሌ፦-

1.ሀ. 

$6 \times 1 = 6$


$1 \times 6 = 6$

ለ. 

$6 \times 7 = 42$


ሐ. 

$6 \times 2 = 12$

መ. 


$3 \times 6 = 18$

$6 \times 3 = 18$

ሠ. 

$4 \times 6 = 24$

$6 \times 4 = 24$

ረ. 

$6 \times 8 = 48$


ምሳሌ፡-

1. ሀ. $5 \times 6 = 30$ መ. $9 \times 6 = 54$
   ለ. $7 \times 6 = 42$ ሠ. $10 \times 6 = 60$
   ሐ. $8 \times 6 = 48$

መልመጃ-2 ሸ

1. ባዶ ቦታውን ሙሉ።

ሀ.



$6 \times 6 = \square$

ለ.



2. የሳጥኑን ዋጋ ሊተካው የሚችል ሙሉ ቁጥር አግኝ።

ሀ. $\square \times 6 = 42$ መ. $6 \times \square = 42$ ሰ. $10 \times \square = 60$
ለ. $\square \times 5 = 54$ ሠ. $5 \times \square = 54$ ሸ. $\square \times 10 = 60$
ሐ. $8 \times \square = 48$ ረ. $\square \times 8 = 48$ ቀ. $4 \times \square = 24$

3. የአንድ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎችን ከጎርፍ ለመጠበቅ 6 ሜትር እኩል ርዝመት ያላቸው 8 እርከኖችን ሰሩ። ተማሪዎቹ የሠሩት የእርከን ርዝመት በጠቅላላው ስንት ሜትር ነው?
4. በተማሪዎች መማሪያ ክፍል ውስጥ 10 አግዳሚ ወንበሮች ይገኛሉ። በእያንዳንዱ አግዳሚ ወንበር ላይ 6 ተማሪዎች ሊቀመጡ ቢችሉ በሁሉም አግዳሚዎች ላይ ስንት ተማሪዎች ሊቀመጡ ይችላሉ?
5. ወ/ሮ ፋጡማ 7 ልጆች አሏት። እያንዳንዳቸው 6 ደብተሮች ያስፈልጋቸዋል።
   ወ/ሮ ፋጡማ በጠቅላላው ስንት ደብተሮች መግዛት አለባት?
6. በ20 እና በ30 መካከል ስንት የ6 ብዜቶች ታገኛላችሁ?

ለ6 ማካፈል


ምሳሌ፡- ሀ)



$12 \div 6 = 2$

ምክንያቱም $6 \times 2 = 12$ ስለሆነ

ለ)




18 ÷ 6 = 3

ምክንያቱም 6 × 3 = 18 ስለሆነ

መልመጃ-2 ኀ

1. የሳጥኑን ዋጋ ፈልጉ::

ሀ.



24 ÷ 4 = ☐

ለ.



2. በምሳሌው መሠረት አስሉ::

ምሳሌ፡- 1

36 ÷ 6 = 6 ምክንያቱም 6 × 6 = 36 ስለሆነ

ሀ. 48 ÷ 6 = ☐ ሐ. 54 ÷ 6 = ☐ ሠ. 72 ÷ 6 = ☐

ለ. 60 ÷ 6 = ☐ መ. 66 ÷ 6 = ☐ ረ. 78 ÷ 6 = ☐

ምሳሌ፡- 2

$48 \div \square = 6$ $\square = 48 \div 6 = 8$

$\square = 8$ ምክንያቱም $6 \times 8 = 48$ ስለሆነ

ሀ. $60 \div \square = 6$ ሐ. $42 \div \square = 6$

ለ. $54 \div \square = 9$ መ. $36 \div \square = 6$

ምሳሌ፡- 3 $\square \div 6 = 5$ $\square = 5 \times 6 = 30$

ሀ. $\square \div 6 = 4$ ሐ. $\square \div 4 = 6$ ሠ. $\square \div 6 = 3$

ለ. $\square \div 6 = 6$ መ. $\square \div 6 = 7$ ረ. $\square \div 6 = 10$

3. አንድ ሀብታም ወላጅ 60 ኪሶችን ለ10 የገጠር ትምህርት ቤቶች እኩል እኩል ቢያከፋፍል እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ስንት ስንት ኪሶች ይደርሱታል?
4. መሐመድ የበዓል ቀን 30 ከረሜላዎች ለ6 ጓደኞቹ እኩል አካፈላቸው። እያንዳንዳቸው ስንት ስንት ከረሜላዎች ይደርሳቸዋል?


በ7 ማባዛትና ማካፈል

ተግባር 2.10

1. 7 የ2 እና የ3 ብዜት ነውን?
2. 7 በ 2 ያለቀሪ ይካፈላልን?
3. በ 0 እና በ20 መካከል የሚገኙትን የ7 ብዜቶች ዘርዝሩ።
4. በ0 እና በ50 መካከል ስንት የ7 ብዜቶችን እናገኛለን። ተማሪዎች በቡድን በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን መልስ ለመምህራችሁ አብራሩ።

ምሳሌ፡-


ሀ.  $1 \times 7 = 7$

ለ. 

$2 \times 7 = 14$



ሐ.




$3 \times 7 = 21$

1	2	3	4	5	6	7*
8	9	10	11	12	13	14*
15	16	17	18	19	20	21*
22	23	24	25	26	27	28*
29	30	31	32	33	34	35*
36	37	38	39	40	41	42*
43	44	45	46	47	48	49*
50	51	52	53	54	55	56*
57	58	59	60	61	62	63*

የ7 ብዜዶች

መ.



$6 \times 7 = 42$

መልመጃ-2 ኘ

1. የሳጥኑን ቦታ ሊተካ የሚችል ሙሉ ቁጥር አግኙ::

ሀ. $\square \times 7 = 70$ ሐ. $7 \times \square = 70$ ሠ. $\square \times 4 = 28$

ለ. $\square \times 8 = 56$ መ. $8 \times \square = 56$ ረ. $4 \times \square = 28$

2. የሳሙኤል እድሜ 7 ዓመት ነው:: የአባቱ የአቶ ከበደ እድሜ የልጁን የሳሙኤልን እድሜ 6 እጥፍ ነው:: የአቶ ከበደ እድሜ ስንት ነው?


3. አቶ አበበ 9 ልጆችን ይረዳሉ:: ለእያንዳንዱ ልጅ 7 ደብተሮች ቢገዙ አቶ አበበ በጠቅላላው ስንት ደብተሮች ገዙ?

ለ7 ማካፈል

ተግባር 2.11


1. በ0 እና በ50 መካከል ለ7 ያለ ቀሪ የሚካፈሉ ስንት ሙሉ ቁጥሮች አሉ?
2. በአንድ ሳምንት ውስጥ ስንት ቀኖች አሉ? በዝርዝር አስረዱ::

ምሳሌ:- ሀ)



21 ÷ 3 = 7 ምክንያቱም 3 × 7 = 21 ስለሆነ

ለ)



ጠቅላላ 35

እያንዳንዱ ምድብ 7 ይዟል

ያሉት ምድቦች 5 ቢሆኑ

35 ÷ 5 = 7 ምክንያቱም 5 × 7 = 35 ስለሆነ

35 ÷ 7 = 5 ምክንያቱም 7 × 5 = 35 ስለሆነ

ሐ) 7 ÷ 7 = 1 ምክንያቱም 7 × 1 = 7 ስለሆነ

14 ÷ 7 = 2 ምክንያቱም 7 × 2 = 14 ስለሆነ


21 ÷ 7 = 3 ምክንያቱም 7 × 3 = 21 ስለሆነ

28 ÷ 7 = 4 ምክንያቱም 7 × 4 = 28 ስለሆነ

35 ÷ 7 = 5 ምክንያቱም 7 × 5 = 35 ስለሆነ

1. ባዶ ቦታውን ሙሉ::






እነዚህን ሙዞች ለ7 ሰዎች እኩል አካፍሉ

42 ÷ 7 = _____

አንድ ሰው ስንት ሙዝ ደረሰው?

ለ)



28 ÷ 7 = ☐

2. የሚከተሉትን በምሳሌው መሠረት አካፍሉ::

ምሳሌ:- 63 ÷ 7 = 9 ምክንያቱም 7 × 9 = 63

ሀ. 70 ÷ 7 = ☐ ለ. 56 ÷ 7 = ☐ ሐ. 42 ÷ 7 = ☐ መ. 35 ÷ 7 = ☐

3. የሳጥኑን ዋጋ አስሉ::

ሀ. ☐ ÷ 7 = 7 ለ. ☐ ÷ 7 = 21 ሐ. 77 ÷ ☐ = 7

4. የአንድ መፅሐፍ ዋጋ 7 ብር ነው:: በ42 ብር ስንት መፅሐፍት መግዛት ይቻላል?

5. 56 ደብተሮችን ለ7 ተማሪዎች እኩል ብናካፍላቸው ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?

በ8 እና በ9 ማባዛትና ማካፈል

ተግባር 2.12

1. የ 8 ብዜቶች የ2 እና የ4 ብዜቶች ሊሆኑ ይችላሉን?
2. ሁሉም የ8 ብዜቶች ለ2 እና ለ4 ያለቀሪ ሊካፈሉ ይችላሉን?
3. 8 የ4 አካፋይ ሊሆን ይችላልን?
4. ሁሉም የ3 እና የ6 ብዜቶች የ9 ብዜቶች ሊሆኑ ይችላሉን? በቡድን ተወያይቡባቸው::


ምሳሌ፦ ሀ.



$2 \times 8 = 16$

$8 \times 2 = 16$

ለ.




$3 \times 8 = 24$

$8 \times 3 = 24$

ምሳሌ፦

ሀ.



ጠቅላላ 32 እየንዳንዱ ምድብ 8 ይዟል።
ምድቦቹ = 4 ቢሆኑ
$32 \div 4 = 8$ ምክንያቱም $4 \times 8 = 32$
ስለሆነ

ለ. $56 \div 8 = 7$ ምክንያቱም $8 \times 7 = 56$

ሐ. $64 \div 8 = 8$ ምክንያቱም $8 \times 8 = 64$


መ. $72 \div 8 = 9$ ምክንያቱም $8 \times 9 = 72$

ሠ. $80 \div 8 = 10$ ምክንያቱም $8 \times 10 = 80$

መልመጃ-2 ከ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥንቃቄ በመመልከት ሣጥኑን ሙሉ።

ሀ.



$5 \times 8 =$ ☐

ለ.

1	2	3	4	5	6	7	8
9	10	11	12	13	14	15	☐
17	18	19	20	21	22	23	☐

2. በምሳሌው መሠረት አስሉ::

ምሳሌ:- $72 \div 8 = \boxed{9}$ ምክንያቱም $8 \times 9 = 72$ ስለሆነ

ሀ. $64 \div 8 = \square$ ምክንያቱም $8 \times \square = 64$

ለ. $48 \div 8 = \square$ ምክንያቱም $8 \times \square = 48$


ሐ. $32 \div 8 = \square$ ምክንያቱም $8 \times \square = 32$

ምሳሌ:-

ሀ. የ9 ብዜት ወይም የ9 ጊዜ ቤት


$1 \times 9 = 9$	$9 \times 1 = 9$
$2 \times 9 = 18$	$9 \times 2 = 18$
$3 \times 9 = 27$	$9 \times 3 = 27$
$4 \times 9 = 36$	$9 \times 4 = 36$
$5 \times 9 = 45$	$9 \times 5 = 45$
$6 \times 9 = 54$	$9 \times 6 = 54$
$7 \times 9 = 63$	$9 \times 7 = 63$
$8 \times 9 = 72$	$9 \times 8 = 72$
$9 \times 9 = 81$	$9 \times 9 = 81$
$10 \times 9 = 90$	$9 \times 10 = 90$
$11 \times 9 = 99$	$9 \times 11 = 99$

ለ.



$5 \times 9 = 45$ ካሬዎች ይገኛሉ::

ሐ.



$9 \times 10 = 90$ ካሬዎች ይገኛሉ::


መልመጃ-2 ወ

1. የሚከተሉትን በጥንቃቄ በመመልከት ሣጥኑን ሙሉ::

ሀ.



ለ.



$8 \times 8 = \square$

2. ሳጥኑን የሚተኩትን ሙሉ ቁጥሮችን አግኙ::

ሀ. $\square \times 9 = 54$ ሐ. $\square \times 9 = 45$ ሠ. $\square \times 6 = 54$

ለ. $\square \times 9 = 63$ መ. $\square \times 5 = 45$ ረ. $\square \times 7 = 63$

ምሳሌ:-

ሀ. $9 \div 9 = 1$ ምክንያቱም $9 \times 1 = 9$ ስለሆነ

ለ. $18 \div 9 = 2$ ምክንያቱም $9 \times 2 = 18$ ስለሆነ

መልመጃ-2 አ

1. በምሳሌው መሠረት አስሉ::

ምሳሌ:- 1. $ሐ \div 9 = 2$

$ሐ = 2 \times 9$

$ሐ = 18$

ሀ. $\square \div 9 = 4$ ሐ. $\square \div 9 = 8$ ሠ. $36 \div \square = 4$

ለ. $\square \div 9 = 7$ መ. $63 \div \square = 7$ ረ. $72 \div \square = 8$

2. የት/ቤታችሁ የስፓርት ክበብ 90 ደብተሮችን ገዝቶ ለ9 ተማሪዎች በስጦታ መልክ አበረከተ:: ለእያንዳንዳቸው ስንት ደብተሮች ይደርሳቸዋል?

የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ::

1. ማንኛውም ሙሉ ቁጥር በዜሮ ሲባዛ ውጤቱ ምንድን ነው?
2. ማንኛውም ሙሉ ቁጥር በአንድ ሲካፈል ድርሻው ስንት ይሆናል?
3. የአንድን ሙሉ ቁጥር እጥፍ ለማግኘት በስንት መባዛት አለበት?
4. በ1 እና በ29 መካከል የሚገኙ የ3 እና የ6 የጋራ ብዜቶችን ዘርዝሩ::
5. በዜሮ እና በ41 መካከል የሚገኙ የ4 እና የ5 የጋራ ብዜቶች የሆኑትን ሙሉ ቁጥሮች ዘርዝሩ?
6. ባዶው ቦታ የሚወክላቸውን ሙሉ ቁጥሮች አሟሉ::
   - ሀ. 7፣ 14፣ ____፣ ____፣ 35፣ _____፣ _____፣ 56
   - ለ. 0፣ 8፣ _____፣ 24፣ 32፣ _____፣ _____፣ 56
   - ሐ. 9፣ 18፣ _____፣ 36፣ _____፣ 54፣ _____
   - መ. 10፣ 20፣ 30፣ _____፣ _____፣ _____፣ 70፣ 80፣ _____፣ _____
7. የሳጥኑን ዋጋ ፈልጉ::
   - ሀ. $30 \div 3 = \square$
   - መ. $77 \div 7 = \square$
   - ቀ. $100 \div 10 = \square$
   - ለ. $40 \div 5 = \square$
   - ሠ. $80 \div 8 = \square$
   - ሐ. $54 \div 6 = \square$
   - ረ. $90 \div 9 = \square$
8. 80 ተማሪዎች በ8 ክፍሎች ውስጥ እኩል እኩል ቢመደቡ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ስንት ተማሪዎች ይገኛሉ?
9. ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ሽልማት ተዘጋጀ:: ከእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ የሚሸለሙት ተማሪዎች ሦስት ሦስት ቢሆኑ ስንት የሽልማት እቃዎች መዘጋጀት አለባቸው?
10. በትምህርት ቤታችህ አዳራሽ ውስጥ እያንዳንዳቸው 8 ወንበሮች የያዙ አስራ አንድ መስመሮች (ረድፎች) ቢኖሩ በአጠቃላይ በአዳራሹ ውስጥ ያሉት የወንበሮች ብዛት ስንት ነው?
11. የሒሳብ መፅሐፋችሁ የገፅ ብዛት 102 ቢሆንና በሳምንት 6 ገፆችን መማር ብትችሉ አጠቃላይ የሒሳብ መፅሐፋችሁን ለመጨረስ ስንት ሳምንቶች ይወስድባችኋል?
12. በቀለ እያንዳንዳቸው 9 የቡና ችግኝ የሚይዙ 11 የአትክልት መደቦች አዘጋጅቷል:: በቀለ በጠቅላላው ስንት የቡና ችግኞችን መትከል ይችላል?
13. የማህሌት እድሜ 9 ዓመት ነው:: የእናቷ እድሜ የማህሌትን እድሜ አራት እጥፍ ነው:: የማህሌት እናት እድሜ ስንት ነው?


ምዕራፍ ሶስት

ልኬት

3.1. ርዝመትን በሳንቲ ሜትርና በሜትር መለካት


ተግባር 3.1

1. የጓደኛችሁ ቁመት ስንት ሳንቲ ሜትር ነው?
2. የደብተራችሁን ርዝመት በማስመሪያ ለኩና ለመምህራችሁ አሳዩ::
3. ማስመሪያ ላይ ያሉትን ሰረዞችና ቁጥሮች በማጥናት ያሏቸውን ግንኙነት ተወያዩ::



ባለአንድ ሜትር ማስመሪያ ወይም 100 ሳንቲ ሜትር ማስመሪያ

የጠረጴዛችሁ ርዝመት 70 ሳንቲ ሜትር ነው




የጠረጴዛችሁ ርዝመት 70 ሳንቲ ሜትር ነው ማለት ነው?

4. የጠረጴዛችሁን ቁመት በቡድን በቡድን በመሆን ለኩ::

አስታውሱ

1. ሜትርና ሳንቲ ሜትር መካከለኛ እና አጫጭር ርቀት ወይም ርዝመት ለመለካት የምንገለገልባቸው ምድቦች ናቸው::
2. ሜትር ባጭሩ ሲፃፍ ሜ ሲሆን ሳንቲ ሜትርን ደግሞ ሳ.ሜ ብለን በመፃፍ መግለጽ እንችላለን::

መልመጃ-3 ሀ



የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሥሩ::


1. የክፍላችሁ ርዝመት በሜትር ስንት ነው?
2. የጥቁር ሰሌዳችሁ ርዝመት በሜትር ስንት ነው?
3. የጠረጴዛችሁን ርዝመትና ቁመት ለኩ:: ስትለኩ መሪያችሁን ተጠቀሙ:: ስንት ሳ.ሜ ነው? በሜትርስ?
4. ከእስኪርፕቶአችሁና ከእርሳሳችሁ የትኛው ረጅም ነው? በምን ያህል ይበላለጣሉ?
5. የሒሳብ መጽሐፋችሁን ርዝመትና ቁመት ለኩና በሳንቲ ሜትር ግለጹ::


3.2. በሳንቲ ሜትር እና በሜትር የተገለፁ ርዝመቶችን መደመርና መቀነስ


ተግባር 3.2

1. የተለያዩ ርዝመት ያላቸውን ነገሮች በአንድ አይነት ምድብ መለካት ይቻላል ወይስ አይቻልም?
2. የተለያዩ ርቀት (ርዝመት) ያሏቸውን ቁሳቁሶች በአንድ አይነት ምድብ በመለካት መደመርና መቀነስ ይቻላል? ተወያዩ::

ለምሳሌ 1:- 50 ሳንቲ ሜትር ገመድ + 40 ሳንቲ ሜትር ሽቦ = 90 ሳንቲ ሜትር ርዝመት እናገኛለን::








ምሳሌ፡-

1. ጀሚላ የ2ኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን ከቤቷ እስከ ትምህርት ቤቷ 100 ሜትር ትጓዛለች። ጀሚላ ደርሶ መልስ ምን ያህል ሜትር ትጓዛለች?



ከት/ቤት እስከ ቤት ያለው ርቀት 100 ሜትር

መልስ፡ ጀሚላ ከት/ቤቷ ወደ ቤቷ የምትጓዘው ርቀት 100 ሜትር እና ከቤቷ ወደ ት/ቤቷ የምትጓዘው ርቀት 100 ሜትር ነው። ደርሶ መልሱን ለማግኘት ሁለቱን ርቀቶች መደመር ይሆናል።

ይኸውም 100 ሜ + 100 ሜ = 200 ሜ

= 200 ሜ ርቀት ተጓዛለች

2. አበራሽ ከአቶ በቀለ ሱቅ 4 ሜትር ርዝመት ያለው ገመድ ገዛች። ከገዛችው ገመድ ላይ አንድ ሜትር ገመድ ቆርጣ እንጨት አሰረችበት። ስንት ሜትር ርዝመት ያለው ገመድ ቀራት?

መልስ፡ ቀሪውን ለማግኘት መጀመሪያ ከነበረው ገመድ ላይ አንድ ሜትር የተጠቀመችበትን መቀነስ እና ማስላት አለብን።

ስለዚህ 4 ሜትር - 1 ሜትር = 3 ሜትር ገመድ ይቀራታል።

3. የአንድ እርሳስ ርዝመት 10 ሳንቲ ሜትር ቢሆን እና ከቀረፃችሁት በኋላ 3 ሳንቲ ሜትር የሚሆነውን ብትጠቀሙበት አሁን የእርሳሳችሁ ርዝመት ስንት ይሆናል?

መልስ፡ አሁን ያለውን የእርሳስ ርዝመት ለማግኘት ከመጠቀማችሁ በፊት ከነበረው የእርሳሳችሁ ርዝመት ላይ የተጠቀማችሁበትን ርዝመት በመቀነስ ማስላት ይቻላል።

ይኸውም 10 ሳ.ሜ - 3 ሳ.ሜ = 7ሳ.ሜ

መልመጃ-3ለ

1. የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. 15 ሜትር + 5 ሜትር

ለ. 75 ሜትር + 10 ሜትር

ሐ. 12 ሳ.ሜ + 13 ሳ.ሜ

መ. 40 ሜ - 10 ሜ

ሠ. 50 ሜ - 20 ሜ

ረ. 70 ሳ.ሜ - 40 ሳ.ሜ

2. የሚከተሉትን የቃላት ኘሮብሌሞች ፍቱ።

ሀ. የክፍላችሁ ርዝመት 4 ሜትር ነው። የክፍላችሁ በረንዳ ርዝመት ደግሞ 2 ሜትር ከ50 ሳ.ሜ ነው። በአጠቃላይ ከክፍላችሁ ጫፍ እስከ ክፍላችሁ በረንዳ ጫፍ ያለው ርቀት ምን ያህል ነው?

ለ. የት/ቤታችሁ የእግር ኳስ ሜዳ ርዝመት 100 ሜትር ሲሆን ወርዱ ደግሞ 50 ሜትር ነው።የትምህርት ቤታችሁን ሜዳ ዙሪያውን ሮጣችሁ ብታጠናቅቁ በጠቅላላው ምን ያህል ርቀት ሮጣችሁ?


ሐ. የኢትዮጵያን አንድ ብር ኖት ቁመቱንና ጎኑን ለኩ።

መ. የትምህርት ቤታችሁን መግቢያ በር ርዝመቱ ለኩ። የምታገኙትን ውጤት በሜትር እና በሳንቲ ሜትር ግለፁ።


3.3 ይዘትን በሊትር መለካት

ተግባር 3.3


1. በቤታችሁ እንደ ውኃ፣ ወተት፣ ዘይትና ሌሎችንም ፈሳሽ ነገሮችን በምን በምን ትለካላችሁ?
2. ተማሪዎች ከቤተሰቦቻችሁ አስፈቅዳችሁ አነስተኛ የፈሳሽ መያዣ ለምሳሌ ሲኒ፣ ብርጭቆ፣ መለኪያ፣ ወዘተ ይዛችሁ መጥታችሁ ክፍል ውስጥ ለምን መስፈሪያ እንደምትጠቀሙባቸውና ይዘታቸውን በመገመት ተወያዩ።
3. ተማሪዎች አንድ ጠርሙስ በግምት ስንት ሲኒ ውኃ መያዝ ይችላል? ሰፍራችሁ አረጋግጡ።




½ ሊትር የሚይዝ ጆግ





1 ሊትር የሚይዝ ጆግ



1 ሊትር የሚይዝ ጠርሙስ







10 ሊትር

የፈሳሽ ይዘት መስፈሪያ መሳሪያዎች (እቃዎች) ናቸው::

ምሳሌ:-

1. ዮሐንስና ማርታ አንድን አነስተኛ ባልዲ ውኃ መሙላት ፈለጉ:: ማርታ 5 ሊትር ውኃ ቀድታ ጨመረች:: ዮሐንስ ደግሞ 7 ሊትር ውኃ ጨመረ እና ባልዲው ሙሉ ሆነ:: የባልዲው የመያዝ አቅሙ ስንት ሊትር ውኃ ነው?

መፍትሔው: ዩሐንስና ማርታ ቀድተው ወደ ባልዲው የጨመሩት ሊትር ብዛት መደመር ይሆናል::

ይኸውም: 5 ሊትር + 7ሊትር = 12 ሊትር ይይዛል ማለት ነው::

2. የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች በምሳ ሰዓታቸው 15 ሊትር የመጠጥ ውሃ ተዘጋጀላቸው:: ከተዘጋጀላቸው 15 ሊትር ውሃ ውስጥ 8 ሊትር የሚሆነውን ብቻ መጠቀም ቻሉ:: ሳይጠቀሙበት የቀረው የውሃ መጠን ምን ያህል ሊትር ነው?

መፍትሔ-: ቀሪውን ለማወቅ መጀመሪያ ከቀረበው የመጠጥ ውሃ መጠን ላይ የተጠቀሙት መጠን መቀነስ ይሆናል:: ይኸውም

15 ሊትር - 8 ሊትር = 7ሊትር ቀሪ ይሆናል ማለት ነው::

አስታውሱ

ሊትር ባጭሩ ሲፃፍ "ሊ" ተብሎ ይፃፋል።

ምሳሌ፡- 25 ሊትር = 25 ሊ፣ 10 ሊትር = 10 ሊ፣ 1/2 ሊትር = ½ ሊ፣ ወዘተ

3.4 በሊትር የተገለፁ ይዘቶችን መደመርና መቀነስ

ተግባር 3.4

1. ተማሪዎች በቤታችሁ የሚገኝ የውኃ ማጠራቀሚያ ባልዲ ወይም እንስራ ስንት ሊትር የሚይዝ ይመስላችኋል? ከባልዲ ወይም ከእንስራ ሌላ በየቤታችሁ ውኃ የሚጠራቀምበትን እቃ ዘርዝሩ። ይዘታቸውንም በመገመት ተወያዩባቸው።
2. አንድ በርሜል፣ ስንት ባልዲ ወይም ስንት ጀሪካን ውሀ ያህል እንደሚይዝ ገምቱ። ከገመታችሁ በኋላ መምህራችሁን ጠይቃችሁ ግምታችሁን አወዳድሩ።
3. ተማሪዎች አንድ ጆግ ወይም አንድ ጠርሙስ ስንት መለኪያ መያዝ እንደሚችል በተግባር ውኃውን በመለኪያ በመቅዳት ወደ ጆጉ ወይም ጠርሙሱ በመገልበጥ አረጋግጡ። የመምህራችሁን ድጋፍ መጠየቅ ትችላላችሁ።

እስከ አሁን የተለያዩ የፈሳሽ መጠን (ይዘት) የሚለውን በዋናነት አይተናል። አሁን ደግሞ የተለያዩ የፈሳሽ መጠኖችን መደመርና መቀነስን እናያለን።



20 ሊትር ውኃ 20 ሊትር ውኃ 20 ሊትር ውኃ

20 ሊ + 20 ሊ + 20 ሊ = 60 ሊ

ሶስቱን ባልዲ በአንድ በርሜል ውስጥ ብንጨምር በጠቅላላው በርሜሉ ውስጥ ስንት ሊትር ውኃ ይኖረናል?

ምሳሌ፡-

መሰለች 3 ሊትር የኑግ ዘይት፣ 5 ሊትር የሰሊጥ ዘይት እና 2 ሊትር የአትክልት ዘይት ገዛች። በጠቅላላው ስንት ሊትር ዘይት ገዛች?

መፍትሔ፡- መሰለች በጠቅላላ ያላትን ዘይት መጠን ለማወቅ የሦስቱንም አይነት የዘይት መጠኖች መደመር ይሆናል።




3ሊ + 5ሊ + 2ሊ = 10ሊ ገዛች ማለት ነው።

ምሳሌ፡-

በቀለች 15 ሊትር ውኃ ከቧንቧ ቀዳች። ከቀዳችው ውኃ ውስጥ 6 ሊትር የሚሆነውን ለምግብ ማብሰያና ለመጠጥ ተጠቀመች። በቀለች ስንት ሊትር ውኃ ይቀራታል?

መፍትሔ፡- በቀለች የቀራትን የውኃ መጠን ለማወቅ ከነበራት 15 ሊትር ላይ 6 ሊትር መቀነስ ወይም ቀሪውን ውሃ መለካት ነው።

15 ሊትር - 6 ሊትር = 9 ሊትር



መልመጃ-3ሐ

1. የሚከተሉትን በምሳሌው መሰረት ሥሩ።

ሀ. 15ሊ + 13ሊ
ሐ. 26ሊ - 15ሊ
ለ. 23ሊ + 24ሊ
መ. 70ሊ - 50ሊ

2. የሚከተሉትን የቃላት ኘሮብሌሞች ፍቱ።

ሀ. አበበ በሳምንት እንቅስቃሴው 8 ሊትር ውኃ ለመጠጥ፣ 8 ሊትር ውኃ ለገላው መታጠቢያና ለመፀዳጃ፣ 10 ሊተር ደግሞ ለልብሶቹ ማጠቢያ ይጠቀማል። የአበበ የሳምንት የውኃ ፍጆታው ስንት ሊትር ነው?

ለ. አየለች ለምግብ ማብሰያና እቃ ማጠቢያ በቀን ሁለት ባልዲ ውኃ ትጠቀማለች። እያንዳንዱ ባልዲ 25 ሊትር ውኃ ይይዛል። አየለች በቀን ስንት ሊትር ውኃ ትጠቀማለች?

ሐ. የአቶ ቴዎድሮስ መኪና በየቀኑ ለምትጓዘው ተመሳሳይ ርቀት 20 ሊትር ነዳጅ ትጠቀማለች። አቶ ቴዎድሮስ በሦስት ቀናት መኪናቸውን ይዘው ለስራ ቢንቀሳቀሱ ስንት ሊትር ነዳጅ ያስፈልጋቸዋል?

መ. ወ/ሮ ንግሥት 25 ሊትር ዘይት በሱቋ ውስጥ አላት። ከዚህ ዘይት ላይ ለወ/ሮ ማህሌት 6 ሊትር እና ለወ/ሮ ብርቱካን 7ሊትር ሸጠች። ወ/ሮ ንግሥት ያልተሸጠ ስንት ሊትር ዘይት ይቀራታል?

3.5. ክብደትን በኪሎ ግራም መለካት

ተግባር 3.5


1. ተማሪዎች ክብደታችሁን በምን እንደምትለኩ ተወያዩበት። የመለኪያው ምድብ ምን ይባላል?
2. ገበያ ወይም ሱቅ ሄዳችሁ ታውቃላችሁ? ካወቃችሁ ስኳር፣ ጨውና ቡና ሰዎች ሲገዙ የሚለኩበት መሳሪያ ምንድን ነው? ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።
3. ሁለት የባትሪ ድንጋዮችን ሚዛን ላይ አስቀምጣችሁ ለኩና ውጤቱን በኪሎ ግራም ግለጹ።
4. ተማሪዎች የራሳችሁ ክብደት ስንት ኪ.ግ እንደሆነ ታውቃላችሁ?
5. የት/ቤታችሁ የእግር ኳስ ክብደት ምን ያህል ነው?
6. የሒሳብ መፅሀፋችሁ ክብደት ምን ያህል እንደሆነ ገምቱ? ሚዛን ካለበት ቦታ ሄዳችሁ በመለካት ግምታችሁንና የለካችሁትን ውጤት አወዳድሩ።

3.6. በኪሎ ግራም የተገለፁ ክብደቶችን መደመርና መቀነስ


ተግባር 3.6

1. ተማሪዎች መጀመሪያ የራሳችሁን ክብደት ተለኩ። ክብደታችሁን መዝግቡ። በመቀጠል ደብተሮቻችሁና መፅሐፍቶቻችሁን ይዛችሁ ተለኩ። ከመጀመሪያው ክብደታችሁ ጋር እኩል ውጤት ታገኛላችሁ? ተወያዩበት።

2. ተማሪዎች ክብደታችሁን ስትለኩ ጃኬቶቻችሁንና ጫማዎቻችሁን አውልቃችሁ ብትመዘኑና ሳታወልቁ ብትመዘኑ የምታገኙት ክብደት ይለያያል ወይስ አንድ አይነት ይሆናል? ተወያዩባቸው::



የሱቅ ሚዛን



- ክብደት ማለት አንድ ነገር በሚዛን ሲመዘን የሚገኘው መጠን ማለት ነው::
- የክብደት መጠን ስንለካ ከምንጠቀምባቸው ምድቦች ውስጥ ኪሎ ግራምና ግራም ይገኙበታል:: ነገር ግን ብዙውን ጊዜ የምንጠቀምበት ምድብ ኪሎ ግራም ነው::
- ኪሎ ግራምን በአጭር አፃፃፍ ስንገልፀው ኪ.ግ በማለት ነው::

ለምሳሌ:- 6 ኪሎ ግራም = 6 ኪ.ግ

- ክብደታቸው ከ1ኪሎ ግራም በታች የሆኑ እንደቀለበት፣ ሐብል፣ የመሳሰሉትን ለመለካት በግራም ከዚህ ሌላ ደግሞ በግማሽ ኪሎ ግራም፣ በሩብ ኪሎ ግራም፣ ወዘተ እንጠቀማለን::

አንድ አይነት ምድብ ያላቸውን የክብደት መጠኖች መደመር ወይም መቀነስ ይቻላል::


ምሳሌ:-

1. አቶ ከበደ 10 ኪ.ግ ስኳር እና 15 ኪሎ ግራም ሩዝ ከአቶ በቀለ ገዛ:: አቶ ከበደ በጠቅላላው የገዛው ስንት ኪ.ግራም ይመዝናል?

መፍትሔ:-

የስኳሩን መጠን እና የሩዙን መጠን መደመር ነው::

10ኪ.ግ + 15 ኪ.ግ = 25 ኪ.ግ



10 ኪ.ግ + 15 ኪ.ግ 25 ኪ.ግ

2. አቶ አምሳሉ የሸቀጣሸቀጥ ሱቅ አለው። ሱቁ ውስጥ 100 ኪ.ግ ስኳር አለው። ካለው 100 ኪ.ግ ስኳር ውስጥ ለደንበኞቹ 60 ኪ.ግ ስኳር መሸጡን ማስታወሻው ላይ መዝግቧል። አቶ አምሳሉ በሱቁ ውስጥ ስንት ኪ.ግ ስኳር ቀረው?


መፍትሔ፦ አቶ አምሳሉ ከነበረው 100 ኪ.ግ ስኳር ላይ ለደንበኞቹ የሸጠውን 60 ኪ.ግራም ስኳር መቀነስ ይሆናል።

ስለዚህ 100 ኪ.ግ - 60 ኪ.ግ = 40 ኪ.ግ ስኳር ሱቁ ውስጥ ይቀራል።

መልመጃ-3መ

1. የሚከተሉትን በጥንቃቄ አስሉና በሳጥኑ ውስጥ ሙሉ።

ሀ. 6 ኪ.ግ + 4 ኪ.ግ = ☐



ለ. 12 ኪ.ግ + 4 ኪ.ግ = ☐

ሐ.15 ኪ.ግ + 24 ኪ.ግ = ☐

2. ወ/ሮ ኤልሳ ክብደታቸው 80 ኪ.ግ ነው። የወ/ሮ ኤልሳ ክብደት መጨመር ለጤንነታቸው ጥሩ አለመሆኑን በመገንዘብ የስፓርት እንቅስቃሴ በማድረግና የአመጋገብ ስርዓታቸውን በማስተካከል 10 ኪ.ግራም ቀነሱ። አሁን የወ/ሮ ኤልሳ ክብደት ስንት ነው?

3. አቶ ከበደ የክብደት ማንሳት ስፓርት ጠዋት ጠዋት ይሰራል። ስለሆነም በቀኝ እጁ 15 ኪ.ግ ክብደት እንዲሁም በግራ እጁ 10 ኪ.ግ ክብደት በአንድ ጊዜ ማንሳት ቻለ። በጠቅላላው አቶ ከበደ ምን ያህል ኪ.ግ ክብደት ማንሳት ቻለ?

የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃዎች

1. *ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ::*

   ሀ. ትልቁ የርዝመት መለኪያ ምድብ ሳንቲሜትር ነው::
   ለ. ወተትን በሊትር መለካት እንችላለን::
   ሐ. ፈላሽ ቁሶችን በሜትር መለካት ይቻላል::
   መ. 1ኪ.ግ ብረትና 1ኪ.ግ ጥጥ እኩል ክብደት አላቸው::

2. *ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ::*

   ሀ. ከሚከተሉት ውስጥ የክብደት መለኪያ ምድብ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ሜ ለ. ሳ.ሜ ሐ. ሊ መ. ኪ.ግ
   ለ. ከፍተኛ ርዝመት ያላቸውን ርቀት ለመለካት የሚያገለግለን ምድብ የትኛው ነው?
   ሀ. ሳ.ሜ ለ. ሜ ሐ. ኪ.ግ መ. ሊ

3. አንድ ባልዲ 25 ሊትር ውኃ መያዝ ይችላል:: ተመሳሳይ ቅርፅ ያላቸው ሁለት ባልዲዎች በድምሩ ስንት ሊትር ውኃ መያዝ ይችላሉ?
4. አቶ ጌታሁን 20 ኪሎግራም ስንዴ እና 24 ኪሎ ግራም ምስር በአህያው ጭኖ ወደ ገበያ ወሰደ:: አቶ ጌታሁን በድምሩ ስንት ኪሎግራም ጥራጥሬ ወደ ገበያ አቀረበ?
5. ወ/ሮ ደመቀች 3 ጀሪካን ዘይት ከሱቅ ገዛች:: እያንዳንዱ ጀሪካን 3 ሊትር ዘይት ይሟል:: ወ/ሮ ደመቀች በጠቅላላው ስንት ሊትር ዘይት አላት?
6. አቶ ታሪኩ 5 የወተት ላሞችን ያረባል:: እያንዳንዳቸው በቀን 10 ሊትር ወተት ይታለባሉ:: የአቶ ታሪኩ ላሞች በድምሩ በቀን ስንት ሊትር ወተት ይታለባሉ?
7. የሚከተሉትን አስሉ

   ሀ. 50 ሜ + 60 ሜ
   ለ. 75 ሜ + 24 ሜ
   ሐ. 60 ሜ + 35 ሜ
   መ. 75 ሳ.ሜ + 25 ሳ.ሜ
   ሠ. 66 ኪ.ግ + 14 ኪ.ግ
   ረ. 82 ኪ.ግ + 18 ኪ.ግ
   ሸ. 80 ሊ + 19 ሊ
   ቀ. 92 ሊ + 8 ሊ

8. የሚከተሉትን አስሉ

   ሀ. 99 ሜ – 19 ሜ
   ለ. 100 ሜ – 20 ሜ
   ሐ. 89 ኪ.ግ – 18 ኪ.ግ
   መ. 76 ኪ.ግ – 29 ኪ.ግ
   ሠ. 92 ሊ – 28 ሊ
   ረ. 86 ሊ – 37 ሊ
   ሸ. 97 ሊ – 49 ሊ

ምዕራፍ አራት

የክፍልፋዮች ፅንሰ ሀሳብ መግቢያ

4.1 ግማሽ እና ሩብ ክፍልፋዮች ክለሳ


ተግባር 4.1

1. ተማሪዎች አንድ ዳቦ ለሁለት መብላት ብትፈልጉ እንዴት ትካፈሉታላችሁ?
2. አንድ የደብተር ሉክ ወረቀት ውሰዱና ጫፍና ጫፉን በማገናኘት እጠፉት። የአጠፋችሁትን ወረቀት ከማጠፊያው ላይ እኩል ለእኩል ቁረጡት። ያገኛችሁት ቁራጭ ወረቀት የአንዱ ሉክ ስንት ስንተኛ ነው?

ምሳሌ፡-




ይህ ወረቀት ሁለት እኩል ለእኩል ተከፍሎ ታዩታላችሁ። ይኸውም የተቀባው ካልተቀባው ጋር እኩል ነው። ስለዚህ የተቀባው አካል ከአጠቃላይ ወረቀቱ ጋር ሲወዳደር ግማሹ ነው። በአሃዝ ሲገለፅ $\frac{1}{2}$ ነው። ሲነበብ አንድ ሁለተኛ ተብሎ ነው።



የተቀቡት ክፍሎች እያንዳንዳቸው የሙሉ ወረቀቱ አንድ አራተኛ (ሩብ) ነው።

አንዱ ክፍልፋይ ሲባዛ $\frac{1}{4}$ ተብሎ ነው። በአንድ ሙሉ ውስጥ አራት ሩቦች አገኘን ማለት ነው።



አንድን ብርቱካን አራት እኩል ቦታ ብንከፍለው የምናገኘው **ሩብ** ወይም **አንድ አራተኛ** ይሆናል።


☺ አስታውሱ

1. የግማሽ መገለጫ ቁጥር $\frac{1}{2}$ ሲሆን ሲነበብም **አንድ ሁለተኛ** በማለት ነው።
2. የሩብ መገለጫ ቁጥር $\frac{1}{4}$ ሲሆን ሲነበብ **አንድ አራተኛ** በማለት ነው።
3. **ክፍልፋይ** ማለት አንድ ሙሉ የሆነን ነገር ወደ ሁለት፣ ወደ ሶስት፣ ወደ አራት እንዲሁም፣ ከዚያ በላይ እኩል በእኩል ስንከፋፍለው ወይም ስንቆርጠው የምናገኘው መጠን ነው።

መልመጃ-4ሀ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ደብተራችሁ ላይ በመፃፍ መልስ ስጡ።

ሀ.  የተቀባው በክፍልፋይ ሲገለጽ _____ ነው።

ለ.  የተቀባው በክፍልፋይ ሲገለጽ _____ ነው።

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጥንቃቄ አስባችሁ በስዕል በመግለፅ መልሱ።

ሀ) አንድ እንጀራን ሁለት ጊዜ እኩል አድራጋችሁ ብታጥፉና ብትቆርሱት ስንት ሩቦችን ወይም $\frac{1}{4}$ ታገኛላችሁ?

ለ) አራት እኩል አንጓ (ቅልጥም) ያሉትን የሽንኮራ አገዳ ለአራት እኩል ቦታ ብትከፍሉት አንዱ አንጓ (ቅልጥም) የሙሉው ስንት ስንተኛ ነው?

ሐ) በአንድ ሙሉ ስንት ግማሾች አሉ?

መ) በአንድ ግማሽ ውስጥ ስንት ሩቦች $\left(\frac{1}{4}\right)$ እናገኛለን?

4.2 ሲሶዎች

ተግባር 4.2


1. ሦስት ጓደኛሞች አንድን የክብ ቅርፅ ያለው ዳቦ እኩል እኩል ቢካፈሉ ለእያንዳንዳቸው የሚደርሳቸው የዳቦ መጠን ስንት ስንተኛው ይመስላችኃል? እስቲ በስዕል ለመሳል ሞክሩ። ተወያዩበት።
2. ተማሪዎች ክፍላችሁ ውስጥ ያለውን ጥቁር ሰሌዳ መምህራችሁ ሦስት ቦታ በጠመኔያቸው ይክፈሉት። ስንት የጥቁር ሰሌዳ ክፍሎች ታያላችሁ? ከተከፈሉት ክፍሎች አንዷን ብቻ ለጽሑፍ ቢጠቀሙበት የጥቁር ሰሌዳውን ስንት ስንተኛውን ተጠቀሙበት ትላላችሁ? ተወያዩበት።

ምሳሌ፡-

አንድ ሙሉ (1) ማስመሪያ

ይህን የሙሉ ማስመሪያ ምስል ሦስት እኩል ቦታ ብንከፍለው እያንዳንዱ ክፍል የሙሉው $\frac{1}{3}$ ኛ ወይም ሲሶ ይሆናል።

$\frac{1}{3}$	$\frac{1}{3}$	$\frac{1}{3}$
ሲሶ	ሲሶ	ሲሶ



ይህ ክብ ሦስት እኩል ቦታ ተከፍሏል። አንዱ ክፍል የክቡ $\frac{1}{3}$ኛ ነው።



የተቀባው የሙሉው 2 ክፍል ነው።

ይህም ሲገለጽ $\frac{2}{3}$ ይሆናል።

$\frac{2}{3}$ ሲነበብ **ሁለት ሦስተኛ ተብሎ** ነው።

☺ አስታውሱ

አንድ ሙሉ ነገር እኩል ሶስት ቦታ ከተከፈለ እያንዳንዱ ክፋይ ሲሶ ወይም አንድ ሶስተኛ ይባላል። ሁለቱ ሲሶዎች በአንድ ላይ ደግሞ $\frac{2}{3}$ ይባላሉ።

መልመጃ-4ለ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምስሎቹን በደብተራችሁ ላይ በመሳል አንድ ሶስተኛ ወይም ሲሶውን አጥቁሩ።


ሀ.



ለ.



ሐ.



መ.



2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በስዕል በመግለፅ መልስ ስጡ።

ሀ. በአንድ ሙሉ ነገር ስንት አንድ ሶስተኛ (ሲሶ) ታገኛላችሁ?

ለ. በአንድ ሙሉ ነገር ውስጥ ስንት $\frac{2}{3}$ ታገኛላችሁ?

4.3 የአንድ ሙሉ ነገር ክፍልፋዮች

ተግባር 4.3


1. አንድን ዳቦ ተከፋፍሎ ብዙ ሰዎች ከሚበሉት እና አንድ ሰው ብቻ ከሚበላው የትኛው ድርሻ ይበልጣል?
2. አንድን ብርቱካን ለሁለት ሰዎች እኩል አካፍሎ ከመስጠትና ለሦስትና ከዚያ በላይ ለሚሆኑ ሰዎች እኩል እኩል አካፍሎ ከመስጠት የየትኛው ድርሻ ይበልጣል? ለምን ተወያዩበት።
3. አንድ ሙሉ ነጭ ወረቀት አውጡ። ጫፍ እና ጫፉን በማጋጠም እኩል በእኩል እጠፉት። አንዱ የታጠፈው ወረቀት የሙሉ ወረቀት ስንት ስንተኛው ነው? ለመምህራችሁ ግለጹ።


   ሁለት ቦታ ያጠፋችሁትን ወረቀት በድጋሜ እኩል በእኩል እጠፉት። የታጠፈበትን ቦታ በእርሳስ አስምሩበት። አንዱን እጥፉት ቀስ አድርጋችሁ ቁረጡት። የቆረጣችሁትን ወረቀት የሙሉ ስንት ስንተኛ ነው? ቀሪውስ? ያከናወናችሁትን በሙሉ ለመምህራችሁ አሳዩ።

4. ተማሪዎች ከአካባቢያችሁ ከሚገኝ ካርቶን ወረቀት ላይ ክብ አክብቡ። ካከበባችሁ በኋላ ክቡን ቆርጣችሁ አውጡ። የክቡን መሀል አግኙ። ከመሀል ነጥብ እኩል ለእኩል ሶስት ቦታ አስምሩ። ካሰመራችሁት አንዱን የክብ ክፍል ቆርጣችሁ አውጡ። የቆረጣችሁት የክቡ ስንት ስንተኛ ነው? ቀሪውስ?

ምሳሌ፡-

በሚከተሉት ምስሎች የተቀቡት ክፍሎች $\frac{1}{2}$፣ $\frac{1}{3}$ ወይም $\frac{1}{4}$ መሆናቸውን ለዩ።

ሀ. 

ለ. 

ሐ. 

መ. 

መልስ


1. በምስል ለ፣ ሐ እና መ ላይ የተቀቡት ክፍሎች ግማሽ ወይም $\frac{1}{2}$ ኛን ይወክሉልናል ::


   በምስል ሀ ላይ የተቀባው ክፍል የሙሉውን $\frac{1}{3}$ኛ ወይም ሲሶ ይወክላል።


   - ሲሶን በአሀዝ ስንገልፀው $\frac{1}{3}$ ብለን ነው። ሲነበብ **አንድ ሶስተኛ** በማለት ነው።
   - ሩብን በአሀዝ ስንገልፀው $\frac{1}{4}$ ብለን ነው። ሲነበብ **አንድ አራተኛ** በማለት ነው።
   - ሦስት ሩቦችን በአሀዝ ስንገልፃቸው $\frac{3}{4}$ ብለን ነው። ሲነበብ **ሶስት አራተኛ** በማለት ነው።
   - ሁለት ሲሶዎችን በአሀዝ ስንገልፃቸው $\frac{2}{3}$ ብለን ነው። ሲነበብ **ሁለት ሶስተኛ** በማለት ነው።

መልመጃ-4ሐ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች የጠቆረውን በማየት ሙሉ፣ ግማሽ$\left(\frac{1}{2}\right)$ ፣ሩብ $\left(\frac{1}{4}\right)$፣ ሲሶ $\left(\frac{1}{3}\right)$፣ $\frac{3}{4}$ እና $\frac{2}{3}$ በማለት መልስ ስጡ።

ሀ. 

ለ. 

ሐ. 

መ. 

ሠ. 

የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ::


1. ሁለት ግማሾች እኩል የሚሆኑት ከየትኛው ጋር ነው?

   ሀ. ከአራት ሩቦች ሐ. ከሶስት ሩቦች

   ለ. ከአንድ ሙሉ መ. ሀ እና ለ

2. ያልተቀባው ክፍል በክፍልፋይ ሲገለፅ የቱ ነው? 

   ሀ. $\frac{1}{4}$ ለ. $\frac{2}{3}$ ሐ. $\frac{1}{3}$ መ. $\frac{3}{3}$

3.  ያልተቀባው ክፍል በክፍልፋይ ሲገለፅ

   ሀ. $\frac{1}{3}$ ለ. $\frac{3}{4}$ ሐ. $\frac{2}{4}$ መ. $\frac{1}{4}$

4.  የተቀባው ክፍል የሙሉውን ስንት ስንተኛ ነው?

   ሀ. $\frac{1}{3}$ ለ. $\frac{1}{2}$ ሐ. $\frac{3}{4}$ መ. $\frac{2}{3}$

5. አራት ግማሾች _____ሙሉ ይሆናሉ::

6. ስምንት ሩቦች _____ ሙሉ ይሆናሉ::

7.  የተቀባው የሙሉው ስንት ስንተኛ ነው?

8.  የልተቀባው የክቡ ስንት ስንተኛ ነው?

9.  የተቀባው የሙሉ ነገሩ ስንት ስንተኛ ነው?

10. 

የምስሉ ጠቅላላ ርዝመት 12 ሳ.ሜ ነው:: ምስሉ በ6 እኩል ተከፍሏል:: ከነዚህ ውስጥ አራቱ ያልተቀቡ ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ የተቀቡ ናቸው:: ስለዚህ የተቀባው ምስል ርዝመቱ ስንት ነው?

ምዕራፍ አምስት

ሙሉ ቁጥሮች እስከ 1000

5.1 የ100 ብዜቶች

ተግባር 5.1 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን በመሆን መልስ ስጡ::

1. ስንት አስሮች መቶ ይሆናሉ?
2. ስንት ሃምሳዎች መቶ ይሆናሉ?
3. መቶ ስንት ዜሮዎች አሉት?
4. መቶ ስንት የአሀዝ ቤቶች አሉት?
5. በ101 እና በ1000 መካከል የሚገኙት የ100 ብዜቶች ስንት ይሆናሉ? ተወያዩባቸው::

ምሳሌ

1. **የሚከተሉትን ተመሳሳይ ዛፎች የያዟቸውን ፍሬዎች ተመልከቱ:: ባዶ ቦታውንም በጥንቃቄ ሙሉ::**


1 × 100 = 100


2 × 100 = 200


3 × 100 = 300


4 × 100 = 400



5×100 = ☐


6 × 100 = ☐


7 × 100 = ☐


8 × 100 = ☐


9 × 100 = ☐


10×100= ☐

ምሳሌ፡-

2. የመቶ ብዜቶችን በቁጥር መስመር ላይ ስናስቀምጥ



ከላይ ያየናቸው የመቶ ብዜቶች በአሃዝና በፊደል ሲገለጽ


ምሳሌ፡-

በአሃዝ	በፊደል
100	መቶ
400	አራት መቶ
700	ሰባት መቶ
1000	አንድ ሺህ

መልመጃ-5ሀ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን ቁጥር በባዶ ቦታው ሙሉ::

ሀ.




3 × 100 = ☐

ለ.



100 + 100 + 100 + 100 = ☐

ሐ.



መ. 1000፣ 900፣ ____፣ ____፣ ____፣ 500፣ 400፣ ____፣ 200፣ ____

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በፊደል ፃፉ::

ሀ. 600 ለ. 100 ሐ. 500 መ. 1000

3. የሚከተሉት በአሃዝ ፃፉ::

ሀ. ሦስት መቶ ሐ. ስድስት መቶ

ለ. ዘጠኝ መቶ መ. ስምንት መቶ

4. የሚከተሉትን ቁጥሮች በምሳሌው መሠረት በመቶ ብዜት ተንትኑ::

ምሳሌ:- 400 = 4 ×100 400 = 100 + 100 + 100 + 100 = 4 × 100

ሀ. 700 ለ. 1000

5. በምሳሌው መሠረት አስሉ::

ምሳሌ:- 1) 100 + 100 + 100 + 100 = 400 =300 + 100

ምክንያቱ 3 + 1 = 4

ሀ. 800 + 100 ለ. 300 + 100

6. የጎደለውን ቦታ ሙሉ::

ሀ. 600 = _____ + 100 ሐ. 200 = 100 +____

ለ.1000 = _____ + 100


5.2. ሙሉ ቁጥሮች ከ101 - 1000

5.2.1 ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር በ100 ብዜቶች ላይ መደመር

ተግባር 5.2

1. 110 የመቶ ብዜት ነውን?
2. አምስት መቶ ሃምሳ ባለ ስንት ሆሄ ቁጥር ነው?
3. አንድ ሺህ ባለ ስንት ሆሄ ቁጥር ነው?
4. የኢትዮጵያን የገንዘብ ኖቶች ታውቃላችሁ? ተወያዩ::

የሚከተለውን ምሣሌ አስተውሉ::





2 x 100 + 1 = 201

200 + 1 = 201






3 x 100 + 5

300 + 5 = <u>305</u>







1 × 100 + 6

100 + 6 = 106 ካሬዎች

6 × 100 + 3

600 + 3 = <u>603</u>

ምሳሌ፡- ሀ. 507 = 500 + 7 = 5 × 100 + 7

ለ. 709 = 700 + 9 = 7 × 100 + 9


ምሳሌ፡-

ሀ. 100 + 1 = 101
200 + 1 = 201

ለ. 200 + 2 = 202
300 + 2 = 302


ሙሉ ቁጥሮችን ከ100 እስከ 1000 በአሃዝና በፊደል ሲገለፁ::

በአሀዝ	በፊደል
101	አንድ መቶ አንድ
110	አንድ መቶ አስር
111	አንድ መቶ አስራ አንድ
112	አንድ መቶ አስራ ሁለት



$5 \times 100 + 5$

$500 + 5 = 505$



$3 \times 100 + 4 \times 10 + 3 \times 1$

$300 + 40 + 3 = 343$


መልመጃ-5ለ

1. የሚከተሉትን አስሉ::

   ሀ. 200 + 5 ለ. 400 + 7


2. በምሳሌው መሰረት በባዶ ቦታው ላይ ሙሉ::

ሀ.




$5 \times 100 + 3 =$ ---------

ለ.



$3 \times 100 + 3 =$ ---------

ሐ.



$3 \times 100 + 7 =$ ----

7

3. የጎደለውን ሙሉ::

ሀ. 505= _____+ 5 ለ. 908 = 900 +_____

4. ሳጥኑን የሚወክለውን ሙሉ ቁጥር አግኙ::

ሀ. ☐ + 5 = 405 ለ. ☐ + 2 = 202

5. ሳጥኑን የሚወክለውን ሙሉ ቁጥር አግኙ::

ሀ. ☐ + 5 = 405 ለ. ☐ + 2 = 202

ሐ. ☐ + 8 = 808 ሠ. ☐ + 1 = 101

መ. ☐ + 1 = 701 ረ. ☐ + 3 = 303

6. የሚከተሉትን ቁጥሮች በፊደል ፃፉ::

ሀ. 403 ሐ. 807 ሠ. 675

ለ. 507 መ. 909 ረ. 995

7. የሚከተሉትን በአሀዝ ፃፉ::

ሀ. አንድ መቶ ሦስት ሐ. አራት መቶ አራት

ለ. ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ መ. ሰባት መቶ አርባ


5.3 እስከ 1000 ያሉ የሙሉ ቁጥሮች የቁጥር ቤት ዋጋ

5.3.1 ሙሉ ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ማስቀመጥ

ተግባር 5.3

1. ባለ አንድ ሆዜ የቁጥር ቤት ስንት ናቸው? ከባለፈው ትምህርታችሁ አስታውሳችሁ ተወያዩ::
2. የቁጥር ቤት እያደገ (እየጨመረ) የሚሄደው ከቀኝ ወደ ግራ ስንሄድ ነው ወይስ ከግራ ወደ ቀኝ? ተወያዩ::
3. የቁጥር ቤት ስንል ምን ማለታችን ነው? ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ::

ምሳሌ:-



ሀ. ከምታዩት አባከስ ውስጥ 4 አስሮች እና 3 አንዶች እንዳሉ ተመልከቱ::

ለ. 725 በቁጥር ቤት ስናስቀምጠው


የመቶ ቤት	የአሥር ቤት	የአንድ ቤት
7	2	5

እያንዳንዱ የቁጥር ቤት አንድን የተሰጠ ሙሉ ቁጥር ለመፃፍ ስንት መቶዎች ስንት አስሮች እና ስንት አንዶችን መጠቀም እንደሚገባን ያመለክታል። ይህንን ቁጥር በአባከስ ስናስቀምጠው እንደሚከተለው ይሆናል።




1. የሚከተሉትን የአባካስ ምስሎች በመጠቀም ትክክለኛውን ቁጥር በሳጥኑ ውስጥ ሙሉ።


ሀ




ሐ.



ለ.



መ.



2. በምሳሌው መሰረት ባዶ ቦታውን ሙሉ።

ሀ. ምሳሌ፦

ሙሉ ቁጥር	የመቶ ቤት	የአስር ቤት	የአንድ ቤት	በፊደል ሲፃፍ
974	9	7	4	ዘጠኝ መቶ ሰባ አራት
623				
236				

3. እያንዳንዱን ቁጥር በቁጥር ቤት ተንትኑ።

ሀ. 345፣ _____የ መቶ ቤት_____ የ አስር ቤት _____የ አንድ ቤት

ለ. 969፣ _____የ መቶ ቤት_____ የ አስር ቤት_____የ አንድ ቤት

መ. 358፣ _____የ መቶ ቤት_____ የ አስር ቤት_____የ አንድ ቤት


5.4 እስከ 1000 ያሉ የሙሉ ቁጥሮች ቅደም ተከተል

ተግባር 5.4

1. ተማሪዎች ቀዳማይ እና ተከታይ ቁጥሮቸን መለየት ትችላላችሁ?
2. የ100 ቀዳማይ ቁጥር ስንት ነው?
3. የ100 ተከታይ ቁጥር ስንት ነው?

ምሳሌ፡-

የሚከተለውን የቁጥር መስመር በደንብ አስተውሉ።



ሀ. የ99 ቀዳማይ ማን ነው?

ለ. የ99 ተከታይ ማን ነው?

ከላይ የተሰጡትን ጥያቄዎች ለመረዳት የቁጥር መስመሩን ተመልከቱ።


ስለዚህ 100 የ99 ተከታይ ሲሆን 98 ደግሞ የ99 ቀዳማይ ነው። ምክንያቱም 99+1=100 ስለሆነና 99-1= 98 ስለሆነ ነው።

ምሳሌ፡-

የ 101 ቀዳማይ እና ተከታይ ስማቸውን ጥሩ።

- የ101 ቀዳማይ ለማግኘት ከ 101 ላይ 1 መቀነስ ስለሆነ
  101 - 1 = 100 ነው ማለት ነው። ስለዚህ የ101 ቀዳማይ 100 ነው።
- የ101 ተከታይ ለማግኘት 1ን በ101 ላይ መደመር ስለሆነ 101 + 1 = 102 ይሆናል። ስለዚህ የ101 ተከታይ 102 ነው ማለት ነው።

5.4.1 ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር



ተግባር 5.5

1. ከላይ የሚታዩትን ስዕሎች ተመልከቱ። ምን ተገነዘባችሁ?
2. ከስዕሉ እንደተረዳችሁት ከሆነ የትኛው ስዕል እኩል ክብደትን ወይም የትኞቹ የሚበላለጡ ክብደቶችን ይገልፃሉ? ተወያዩባቸው።

3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች > (ይበልጣል)፣< (ያንሳል) ወይም = የእኩልነት ምልክቶችን በመጠቀም አወዳድሩ።

1. 567_____667 2. 867_____876 3. 868_____867

አስታውሱ

1. *ምንጊዜም ቢሆን የቁጥር ሆሄያት እኩል የሆነባቸውን ቁጥሮች ስናወዳድር ውድድሩ የሚጀምረው ከትልቁ የቁጥር ቤት ሆሄ ነው። ትልቁ የቁጥር ቤት አንድ አይነት (እኩል) ሆኑ ወደ ሚቀጥለው ትንሽ የቁጥር ቤት በመሸጋገር ማወዳደር እንችላለን።*

2. *የቁጥር ሆሄዎች የሚበዙበት ቁጥር ምን ጊዜም ትልቁ ቁጥር ነው።*

ምሳሌ፡-

1. 436 > 456 ሐሰት ነው። ምክንያም የ10 ቤቱ 3 > 5 ሐሰት ስለሆነ። የመቶ ቤቱና የአንድ ቤቱ ቁጥሮች አንድ አይነት ናቸው።

2. 675 > 98 እውነት ነው። ምክንያቱ የቁጥር ሆሄው ሶስት እና ሁለት ስለሆነ፣ በቀጥታ የቁጥር ቤቱን ስናወዳድር መወሰን እንችላለን።

መልመጃ-5 መ

1. ለሚከተሉት ቁጥሮች የእያንዳንዳቸውን ተከታይ ቁጥሮች ፈልጉ።

ሀ. የ120	ሐ. የ995	ሠ. የ599
ለ. የ155	መ. የ999	ረ. የ609

2. በሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች መካከል የሚገኙትን ሙሉ ቁጥሮች ዘርዝሩ።

ሀ. 672 እና 675	ሐ. 265 እና 271
ለ. 152 እና156	መ. 890 እና 897

3. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች <፣> ወይም = ምልክቶችን በመጠቀም አወዳድሩ።

ሀ) 675 _____673

ለ) 767 _____669

ሐ) 874 _____789

መ) 777 _____775 + 2

4. በሚከተሉት ቁጥሮች የእያንዳንዳቸውን ቀዳማይ ቁጥር ፈልጉ።

ሀ. የ225	ሐ. የ456	ሠ. የ698	ሸ. የ999
ለ. የ340	መ. የ575	ረ. የ798	ቀ. የ907

5. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በማስላት ውጤታቸውን <፣> ወይም = ምልክቶችን በመጠቀም አወዳድሩ።

ሀ. 675 + 12 _____673 + 14

ለ. 767 + 10 _____669 + 12

መ. 898 – 11 _____879 + 10

ሠ. 876 – 25 _____888 – 35

የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

1. ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ::

ሀ. አንድ ሺህ ባለ ሦስት ሆሄ ቁጥር ነው:: መ. የ99 ተከታይ 100 ነው::

ለ. በመቶ ውስጥ 11 አስሮች አሉ:: ሠ. 159 > 161

ሐ. የ87 ቀዳማይ 88 ነው::

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ::

ሀ) ከሚከተሉት ውስጥ እውነት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. 98 < 101 ለ. 122 > 211 ሐ. 400 < 399 መ. 699 > 700

ለ) ከሚከተሉት የ999 ተከታይ የቱነው?

ሀ. 998 ለ. 997 ሐ. 1000 መ. 1001

ሐ) ከሚከተሉት አንዱ የ100 ብዜት አይደለም?

ሀ. 405 ለ. 700 ሐ. 600 መ. 1000

መ) 343 < ሀ < 347 የተለዋዋጩን ዋጋ ሊተካው የሚችለው የቱ ነው?

ሀ. 344 ለ. 345 ሐ. 346 መ. ሁሉም

ሠ) የ110 ተከታይ የቱ ነው?

ሀ. 100 ለ. 111 ሐ. 109 መ. 120

3. በሙሉ ቁጥሮቹ መካከል የሚገኙትን ሙሉ ቁጥሮች ዘርዝሩ::

ሀ. 699 እና 703 ለ. 200 እና 800 (የመቶ ብዜቶችን)

4. የሚከተሉትን ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቁ በቅደም ተከተል አስቀምጡ::

ሀ. 460፣ 604፣ 406፣ 640፣ ለ. 478፣ 484፣ 448፣ 487

5. የሚከተሉትን ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል አስቀምጡ::

ሀ. 673፣ 695፣ 699፣ 697

ለ. 696፣ 701፣ 777፣ 769

ሐ. 860፣ 887፣ 869፣ 884

ምዕራፍ ስድስት

ነጥቦች፣ቀጥታ መስመሮች እና ቅርጾች(ምስሎች)

ተግባር 6.1

1. እርሳሳችሁን ተጠቅማችሁ ሁለት የተለያዩ ነጥቦችን አመልክቱ።
2. በመቀጠል እነዚህን ነጥቦች በፊደል ሰይሟቸው።
3. ማስመሪያ በመጠቀምና በማስመር ሁለቱን ነጥቦች አገናኟቸው። ምን አገኛችሁ?

6.1 ማስመሪያን በመጠቀም ቀጥታ መስመሮችን መሣል

ምሳሌ፦



ሀ እና ለ ነጥቦች ናቸው።
ሁለቱን ነጥቦች ማስመሪያ ተጠቅመን ብናገናኛቸው የሚከተለውን ምስል እናገኛለን።



ስያሜውም ውስን ቀጥታ መስመር ሀለ ወይም ውስን ቀጥታ መስመር ለሀ ይባላል።
በፅሁፍ $\overline{\text{ሀለ}}$ በማለት እንገልፃለን።

1. ነጥቦች ምንጊዜም የሚሰየሙት በፊደላት ነው።


   ምሳሌ፦

   •ሀ ነጥብ ሀ

   •ለ ነጥብ ለ

2. ቀጥታ መስመር የሚሰየመው በላዩ ላይ በሚገኙ ሁለት ነጥቦች ነው።


   ምሳሌ፦



6.1.1 የነጥቦችና የመስመሮች ግንኙነት

ተግባር 6.2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ መልስ ስጡ።



1. ሀ) ቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{ሀለ}$ በነጥብ _____ላይ ያልፋል።

   ለ) ቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{ሠረ}$ በነጥብ _____ላይ ያልፋል።

   ሐ) ነጥብ 'መ' የ _____እና_____ መቋረጫ ነው።


   መ) ነጥብ _____የመቋረጫ ነጥብ ተብሎ ይጠራል።

   ሠ) ነጥብ መ በነጥብ _____እና _____ መካከል ይገኛል።

   ረ) $\overleftrightarrow{ሀለ}$ በነጥብ _____ላይ ያልፋል።

   ሸ) $\overleftrightarrow{ሠረ}$ በነጥብ _____ላይ ያልፋል።

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።



ሀ. በነጥብ 'መ' ላይ ስንት መስመሮች አልፈዋል?

ለ. በነጥብ 'መ' ላይ ስንት መስመሮች ማለፍ ይችላሉ?

ሐ. በነጥብ 'መ' ላይ የሚያልፉትን ቀጥታ መስመሮች በሙሉ ዘርዝሩ።

3. በተሰጡ ሁለት ነጥቦች ላይ ስንት ቀጥታ መስመር መስራት ትችላላችሁ?


•ሀ •ለ

4. የሚከተሉትን ነጥቦችና ቀጥታ መስመሮች ተመልከቱ።

ሀ) ነጥብ 'ተ' ከቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{\text{መነ}}$ _____ክፍል ይገኛል።


ለ) ነጥብ 'ቀ' ደግሞ ከቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{\text{መነ}}$ _____ ክፍል ይገኛል።

ሐ) ነጥብ 'ረ' ቀጥታ መስመር _____ ላይ ይገኛል።



መልመጃ- 6ሀ

ከዚህ በታች የተቀመጡትን በመመልከት ከተራ ቁጥር 1 - 7 የተሰጡ ባዶ ቦታዎች ሙሉ።



1. ጨ ፣ ጀ፣ _____፣ _____፣ _____ እና _____ በመስመር ያልተገናኙ ነጥቦች ናቸው።
2. _____ እና _____ውስን ቀጥታ መስመሮች ናቸው።
3. _____፣_____፣_____እና_____የውስን ቀጥታ መስመሮች ጫፍ ናቸው።
4. _____፣ _____፣ _____ እና _____ በቀጥታ መስመሮች ላይ የሚገኙ ነጥቦች ናቸው።
5. ጨ እና ጀ ን በማገናኘት የምንሠራው ውስን ቀጥታ መስመር _____ ነው።
6. ጀ እና ሠን በማገናኘት የምናገኘው ውስን ቀጥታ መስመር _____ ነው።
7. ፈ እና ቀ ን በማገናኘት የምናገኘው ውስጥ ቀጥታ መስመር _____ ነው።
8. ሁለት ነጥቦችን ወስዳችሁ በፊደሎች ካመለከታችሁ በኋላ በእነሱ ላይ የሚያልፍ ቀጥታ መስመር በማስመሪያ በመጠቀም ሳሉ። ቀጥታ መስመሩን ሰይሙ።


9. በ8ኛ ጥያቄ ላይ ከሳላችሁት ቀጥታ መስመር ላይ በሚገኙ ሁለት ነጥቦች መካከል የሚገኘው ውስን ቀጥታ መስመር ምን ተብሎ ይጠራል? ውሰን ቀጥታ መስመሩን በፅሁፍ ምልክት ግለጹ።

መልመጃ- 6ለ


1. ከዚህ በታች የተሰጠውን ምስል በመጠቀም ጥያቄዎችን መልሱ።



ምስል 1



ምስል 2



ምስል 3


ሀ. ምስል 1 _____ ነው።

ለ. ምስል 2 የመቋረጫ ነጥብ _____ ነው።

ሐ. በምስል ሶስት _____ ነው።

2. የሚከተሉትን ቀጥታ መስመሮችና ውስን ቀጥታ መሥመሮችን ሰይሙ።

ሀ.




ለ.




ሐ.



መ.



ሠ.



3. የሚከተሉትን ሳሉና ሰይሙ።

ሀ. ውስን ቀጥታ መስመር $\overline{ጨደ}$ ሐ. ውስጥ ቀጥታ መስመር $\overline{ሀለ}$

ለ. ቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{ደቸ}$ መ. ቀጥታ መስመር $\overleftrightarrow{ቀበ}$

4. በነጥብ ረ ላይ የሚያቋርጡ ሁለት ቀጥታ መስመሮችን ሳሉና ሰይሙ።

5. ሁለት የሚያቋርጡ ቀጥታ መስመሮችን ሳሉ። የሚያቆሙበትን ቦታ ቀ ብላችሁ ሰይሙ።

6. የሚከተሉትን ውስን ቀጥታ መስመሮች ርዝመታቸውን አወዳድሩ::



ሀ. ከ $\overline{\text{ጨደ}}$ እና ከ $\overline{\text{ጠየ}}$ የቱ ይረዝማል?

ለ. ከ $\overline{\text{ጨደ}}$ እና ከ $\overline{\text{ገቸ}}$ የቱ ይረዝማል?

ሐ. ከ $\overline{\text{ጨደ}}$ እና ከ $\overline{\text{ጠየ}}$ የቱ ያንሳል?

መ. ከ $\overline{\text{ጠየ}}$ እና ከ $\overline{\text{ገቸ}}$ የቱ ይረዝማል?

ሠ. ከሁሉም ረዥሙ ውስን ቀጥታ መስመር የቱ ነው?

ረ. ሁሉንም ውስን ቀጥታ መስመሮች በማስመሪያ ለኩና አግኙ::

6.2 ጎነ አራት፣ ካሬ፣ ጎነ ሦስት እና ክብ ምስሎች

ተግባር 6.3


የሚከተሉትን የወለል ምስሎች ስም በባዶ ቦታው ላይ ሙሉ::

1. 


ጎነ _____ ነው::

3. 

ጎነ _____ ነው::


2. 

_____ ነው::

4. 

አራቱም ጎኖች እኩል ናቸውን? ማስመሪያ ተጠቅማችሁ ለኩ::

5. በአካባቢያችሁ ወይም በቤታችሁ ከሚገኙት እቃዎች የትኞቹ ይመሳሰላሉ? እየዘረዘራችሁ ተወያዩባቸው?

6. 

የሚመሳሰሉ ቅርፆችን አንድ አይነት በመቀባት ሦስት የተለያዩ ቀለሞችን ተጠቀሙ። ለመምህራችሁ አሳዩ።

7. ርዝመቱ 4 ሳንቲ ሜትር ቁመቱ 3 ሳንቲ ሜትር የሆነ ጎነ አራት ምስል ሳሉ።


8. ርዝመቱ 6 ሳንቲ ሜትር የሆነ ጎነ ሦስት ምስል ሳሉ።

6.2.1 ጎነ ሦስት እና ጎነ አራት ምስሎች


1. ይህ ጎነ ሦስት ምስል ነው።

   - ጎነ ሦስት ፈከመ ተብሎ ይጠራል።
   - በአጭሩ ሲጻፍ △ፈከመ ይሆናል።

   △ የጎነ ሦስቱ መገለጫ ምልክት ነው።



ጎነ ሦስት ምስል




$\overline{\text{ፈመ}}$ ፣ $\overline{\text{መከ}}$ እና $\overline{\text{ፈከ}}$ የጎነ ሶስት ፈከመ ጎኖች ናቸው።

2. የተቀባው **የጎነ ሦስት ፈከመ ወለል** ነው።

ከላይ በጎነ ሦስት ምስል እንዳየነው የባለ ጎነ አራትንም ምሥል ባሕርይ እንመልከት።

ቀጥሎ ያለው ምስል የሚታየው **ጎነ አራት** በመባል ይጠራል።




ጎነ አራት ምስሎች በመለያያቸው ላይ በሚገኙ ነጥቦች ስያሜ ላይ በመመስረት ይሰየማሉ።

ምሳሌ፡-

በውስን ቀጥታ መስመሮች $\overline{መነ}$፣ $\overline{ተቀ}$፣ $\overline{መተ}$ እና $\overline{ነቀ}$ የተሠራው ጎነ አራት **ቀነመተ** ተብሎ ይሠየማል።


1. ይህ ምስል ጎነ አራት **ተቀነመ** ተብሎ ይጠራል። ጎነ አራቱ በሌሎች ስያሜዎች ሊጠራ ይችላል።



ምሳሌ፡- ተቀነመ፣ መነቀተ፣ ነቀተመ በመባል መሠየም ወይም መጥራት ይቻላል።

➢ $\overline{መነ}$፣ $\overline{ነቀ}$፣ $\overline{ቀተ}$ እና $\overline{ተመ}$ የ'ተቀነመ' ጎኖች ናቸው።

6.2.2 ካሬ



በምስሉ የሚታየው አራቱም ጎኖቹ በርዝመት እኩል የሆነ ጎነ አራት ምስል ሲሆን **ካሬ** በመባል ይጠራል።
የተቀባው የጎነ አራት (ካሬ) **ሀለመሠ** **ወለል** ወይም **ጠለል** ነው።

የቡድን ሥራ


1. ርዝመቱ 3 ሳ.ሜ የሆነ ካሬ ሳሉ።
2. ርዝመቱ 5 ሳ.ሜ የሆነ ካሬ ሳሉ። ዙሪያው ስንት ሳንቲ ሜትር ይሆናል?

6.2.3 ክብ

ተግባር 6.4

ተማሪዎች፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጋራ ተወያዩባቸው።

1. ከአካባቢያችሁ በሚገኝ እንደ ጣሳ፣ ሳንቲም፣ የልብስ ቁልፍ ወይም የክብ ቅርጽ ፈልጋችሁ በእርሳስ አክብቡ። ምን አገኛችሁ? ለመምህራችሁ አሳዩ።



በክቡ ላይ የተመለከቱት ነጥቦች ዘ፣ ፈ፣ ጠ፣ የ፣ ነ እና መ ሌሎቹም ነጥቦች ከመሀል ነጥብ ‘ወ’ እኩል ርቀት ላይ ይገኛሉ።

መልመጃ- 6ሐ

. ጠ . የ . አ

.መ

. ዘ .ፈ .ነ

1. በነጥቦች ጠ እና የ የሚያልፍ ስንት ቀጥታ መስመሮች መሳል ይቻላል?
2. ነጥብ መ እና ነ በውስን ቀጥታ መስመር ስታገናኙ የሚፈጠረው ምን ይባላል?
3. ነጥቦች መ፣ነ እና አ በውስን ቀጥታ መስመሮች ስታገናኙ የምታገኙት (የሚፈጠረው) ምስል ምን ይባላል?
4. ነጥቦች ጠ፣የ፣ፈ፣ እና ዘ በውስን ቀጥታ መስመሮች ስታገናኙ የምታገኙት ምስል ምን ይባላል?
5. ነጥቦች የ፣ ፈ፣ ነ፣ እና አ በውስን ቀጥታ መስመሮች ስታገናኙ የምታገኙት ምስል ምን ይባላል?



6. የ $\overline{ሀለ}$ እና የ$\overline{ለሐ}$ መለያያ ነጥብ የትኛው ነው?
7. ጎነ ሦስት ምስል ሥሩ። መለያያዎቹን ጎኖቹን ሰይሙ። በምስሉ ላይ ወለሉን አመልክቱ።
8. ጎነ አራት (ሬክታንግል) ምስል ሥሩ። መለያያዎቹንና ጎኖቹን ሰይሙ።
9. ጎነ አራት (ካሬ) ምስል ሥሩ። መለያያዎቹን እና ጎኖቹን ሰይሙ።
10. የክብ ምስል ሥሩና ሰይሙ። ወለሉን አሳዩ።
11. በክብ መሳያ ከመሀሉ 2 ሳ.ሜ. ርቀት ያለው ክብ ሥሩ።
12. ነጥብ ወን አመልክቱ። ወን መሀል በማድረግ በክብ መሳያ ክብ ሥሩ።

6.3 በአካባቢያችን የሚገኙ ምስሎች (ቅርጾች)

ተግባር 6.5


የሚከተሉትን ምስሎች ስም ጥሩ።

ሀ. 


_____

ሐ. 


_____

ሠ. 

_____

ለ. 


_____

መ. 


_____

ምሳሌ፡-

የናፍጣ ወይም የዘይት መቅጃ ማንቆርቆሪያ ምን ቅርጽ አለው? ቅርጹ የክብና የክብ ክፋይ ውህድ ነው።



ምሳሌ፡-



የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

1. ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ::

ሀ. ጎነ ሦስት አራት መለያያ ነጥቦች አሉት::

ለ. ማንኛውም ጎነ አራት ካሬ መሆን ይችላል::

መ. ነጥብ መሠረታዊ የጂኦሜትሪ መነሻ ነው::

ሠ. ውስን ቀጥታ መስመሮች ቀጥታ መስመሮች መሆን ይችላሉ::

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ::

ሀ. ከሚከተሉት አንዱ አራት መለያያዎች አሉት::

ሀ. ክብ ለ. ጎነ ሦስት ሐ. ጎነ አራት

መ. ካሬ ሠ. ሐ እና መ

ለ. ከሚከተሉት አንዱ መለያያ ነጥብ የለውም::

ሀ. ጐነ-ሦስት ለ. ካሬ ሐ. ሬክታንግል መ. ክብ

ሐ. ውስን ቀጥታ መስመርን መሠየም የምንችለው በስንት ፊደል ነው?

ሀ. በአንድ ለ. በሁለት ሐ. በሦስት መ. በአራት

መ. የጥቁር ሰሌዳ ቅርጽ የሚመደበው በየትኛው ነው?

ሀ. ከጎነ ሦስት ለ. ከጎነ አራት ሐ. ከክብ

3. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ::

ሀ. ጎነ አራት ምስልን ለመስራት ስንት ውስን ቀጥታ መስመሮች ያስፈልጉናል?

ለ. ጎነ ሶስት ምስልን ለመስራት ስንት ውስን ቀጥታ መስመሮች ያስፈልጉናል?

ሐ. የዘይት መቅጃ ማንቆርቆሪያ የምንና የምን ቅርፅ ውህድ ነው?

መ. የሲሊንደር ቅርፅ የምንና የምን ውህድ ነው?

ሠ. አራቱም ጎኖች እኩል ርዝመት ያለው ጎነ አራት ምስል ምን ይባላል?

ረ. በአካባቢያችሁ ከሚገኙ እቃዎች ጎነ አራት ቅርፅ ያላቸውን ዘርዝሩ::

ምዕራፍ ሰባት

ገንዘብ

7.1 ገንዘብን መደመርና መቀነስ

የቡድን ሥራ

1. የኢትዮጵያ የመገበያያ ገንዘብ ምን ይባላል?
2. ተማሪዎች እስከ አሁን የባለ ስንት ብር ኖት አይታችኋል?
3. በሳንቲም ደረጃ የትኞቹን የሳንቲም ዲናሮች ታውቃላችሁ?
4. የኢትዮጵያን የመገበያያ ሳንቲም ዲናሮች አይነት ዘርዝሩ።
5. የኢትዮጵያን መገበያያ የብር ኖቶች ዘርዝሩ።

ገንዘብ ማለት ሕዝቦች በመግባባት እቃዎችን ወይም አገልግሎትን የሚገዙበት የብር ኖቶች ወይም የሳንቲም ዲናሮች ነው። የብሮቹና የሳንቲሞቹ የዋጋ መጠን የተለያዩ ናቸው። በመንግሥት የሚታተሙ ናቸው። በዚህም መሠረት **ባለ መቶ ብር፣ ባለ ሃምሳ ብር፣ ባለ አሥር ብር፣ ባለ አምስት ብር** እና **ባለ አንድ ብር የወረቀት ብር** ወይም **ኖቶች** አሉን። በሳንቲም ደረጃ ደግሞ **ባለ አንድ ብር፣ ባለ ሃምሳ ሳንቲም፣ ባለ ሃያ አምስት ሳንቲም፣ ባለ አሥር ሳንቲም፣ ባለ አምስት ሳንቲም** እና **በባለ አንድ ሳንቲም ዲናሮች** አሉን።



የ1 ብር ኖት




የ5 ብር ኖት



የ10 ብር ኖት



የ50 ብር ኖት



የ100 ብር ኖት



1ሳንቲም 5ሳንቲም 25 ሳንቲም 50 ሳንቲም 1 ብር


የኢትዮጵያ የመገበያያ የሳንቲም ዲናሮች

ለምሳሌ፡-

1. (ሀ) አንድ የመቶ ብር ኖት ስንት ባለ ሃምሳ ብር ኖት ይሆናል?

100 ብር = 2 ባለ ሃምሳ ብር ኖት ነው።

ምክንያቱም 2 × 50 ብር =100 ብር ስለሆነ



(ለ) የ50 ብር ኖት ባለ ስንት የአሥር ብር ኖት ይሆናል?



50 ብር = 10 ብር + 10 ብር + 10 ብር + 10 ብር + 10 ብር

ስለዚህ 5 ባለ አሥር ብር ኖቶች አንድ ባለ ሃምሳ ብር ኖት ይሆናል ማለት ነው።

(ሐ) የ10 ብር ኖት ባለ ስንት አምስት ብር ኖቶች ይሆናል?




10 ብር = 5 ብር + 5 ብር

ወይም 10 ብር = 2 × 5 ብር ይሆናል።

10 ብር = 10 ብር ስለዚህ ሁለት ባለ አምስት ብር ኖቶች አንድ ባለ አሥር ብር ኖት ይሆናል ማለት ነው።

መ. የ5 ብር ኖት ስንት ባለ አንድ ብር ኖት ይሆናል?



5 ብር = 1ብር + 1 ብር + 1 ብር + 1 ብር + 1ብር

☺ **አስተውሉ**

1. ሀ. አንድ የ100 ብር ኖት በ2 ባለ 50 ብር ኖቶች



ለ. አንድ የ100 ብር ኖት = በ10 ባለ 10 ብር ኖቶች



ሐ. አንድ የ100 ብር ኖት = 20 ባለ 5 ብር ኖቶች



መ. አንድ የ100 ብር ኖት በ100 ባለ 1 ብር ኖቶች ይመነዘራል።

2. እያንዳንዱ የብር ኖቶች በላያቸው ላይ በተጻፉት አሀዞች ልክ ዋጋ አላቸው። በተጨማሪ እያንዳንዳቸው የተለያዩ ቀለም፣ ቅርጽ እንዲሁም ስዕሎች አሏቸው። በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ለዩ።

3. ማንኛውም የመገበያያ ገንዘብ በአገሪቱ መንግሥት እውቅና (ባለቤትነት) ብቻ ታትመው ገበያ ላይ ይውላሉ።

4. የኢትዮጵያ ገንዘብ ምድቦች ብር እና ሳንቲም ናቸው። የተለያዩ አገሮች የመገበያያ ገንዘብ ምድቦች የተለያዩ ናቸው።

ምሳሌ፡-

የ1ብር ኖት በስንት የ50 ሳንቲምና በስንት ባለ 25 ሳንቲም ዲናር ይመነዘራል?

1ብር = 100 ሳንቲም ነው።

100 ሳንቲም = 2 × 50 ሳንቲም

= 50 ሳንቲም + 50 ሳንቲም (2 ባለ ሃምሳ ሳንቲም)

= 25 ሳንቲም + 25 ሳንቲም+ 25 ሳንቲም+ 25 ሳንቲም


= 4 × 25 ሳንቲም (አራት ባለ 25 ሳንቲም) ይሆናል።



= 1 ብር ከ25 ሳንቲም

100 ሳንቲም = 1 ብር

ለ. 45 ብር – 13 ብር



4 ባለ 10 ብር ኖቶች እና

እና



5 ባለ 1 ብር ኖቶች



45 ብር
ወይም -13 ብር
32 ብር

7.2 ግብይት


ተግባር 7.1

1. ተማሪዎች አንድ እርሳስ እና እስኪሪብቶ በስንት ሳንቲም ትገዛላችሁ?
2. ላጲሳችሁን በስንት ባለ 10 ሳንቲሞች ገዛችሁ?
3. የእርሳስ መቅረጫችሁን በስንት ብር ወይም ሳንቲም ገዛችሁ? ተወያዩ።
4. አንድ የስዕል ነጭ ወረቀት በስንት ሳንቲም መግዛት ትችላላችሁ?
5. ቤተሰቦቻችሁ ገበያ ወይም ሱቆች ሄደው ምን ምን ይገዛሉ? የሚገበያዩበት ገንዘብ ባለ ስንት የብር ኖቶች እና ሳንቲሞች ናቸው? ቤተሰብ በመጠየቅ በሳንቲም ሊገዙ የሚችሉትን የእቃዎች ዝርዝር ለብቻ በብር ኖቶች እና በሳንቲም ዲናሮች ሊገዙ የሚችሉትን የእቃ ዝርዝር ለብቻቸው በመለየት ዘርዝሩ። ተወያዩባቸው።

ምሳሌ፡-

ሀ. አንድ ብርቱካን 75 ሣንቲም ቢሸጥ አራት ተመሳሳይ ብርቱካኖች ለመግዛት ስንት ብር ያስፈልገናል?

75 ሳንቲም + 75 ሳንቲም + 75 ሳንቲም + 75 ሳንቲም



4 ሀምሳ ሳንቲሞች እና አራት 25 ሳንቲሞች

4 ሃምሳ ሳንቲሞች = 2 ብር 4 ባለ 25 ሳንቲሞች=1ብር

በጠቅላላው 2 ብር + 1 ብር = 3 ብር ያስፈልገናል።

ለ. ከዚህ በታች በምስሉ ላይ የሚታዩት ሳንቲሞች ስንት ብር ናቸው?



2 ብር ከ65 ሣንቲም

1. አቶ ሳምሶን ገበያ ሄዶ ከአቶ አማረ በ1000 ብር ሁለት በጎችን ገዛ። አቶ ሳምሶን ለአቶ አማረ ስንት ባለ መቶ ብር ኖት መክፈል አለበት?

10 × 100 = 1000 ብር

10 ባለ መቶ ብር ኖቶችን መክፈል አለበት



መልመጃ-7ሀ

1. የሚከተሉትን ደምሩ።

1. ሀ. 10 ብር + 25 ብር
   ለ. 12 ብር + 5 ብር
   ሐ. 50 ብር + 6 ብር
   መ. 60 ብር + 40 ብር
   ሠ. 50 ብር + 50 ብር
   ረ. 100 ብር + 200 ብር

2. ሀ. 25 ሳንቲም + 75 ሳንቲም ሐ. 35 ሳንቲም + 10 ሳንቲም
ለ. 10 ሳንቲም + 40 ሳንቲም መ. 55 ሳንቲም + 25 ሳንቲም

3. የሚከተሉትን ቀንሱ::

1. ሀ. 25 ብር - 10 ብር ሐ. 65 ብር - 15 ብር
ለ. 50 ብር - 40 ብር መ. 70 ብር - 20 ብር

2 ሀ. 90 ሳንቲም - 80 ሳንቲም ሐ. 100 ሳንቲም - 85 ሳንቲም
ለ. 95 ሳንቲም - 15 ሳንቲም መ. 150 ሳንቲም - 100 ሳንቲም

4. የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌምች ፍቱ::

ሀ. አዝመራው ለሁለት ልጆቹ 10 ደብተሮች እያንዳንዳቸውን በ3 ብር ከሱቅ ቢገዛ በጠቅላላው ስንት ብር ከፈለ? በሳንቲም ሲመነዘርስ?

ለ. አልማዝ ከአቶ ሀሰን መደብር 1 ኪሎ ስኳር በ15 ብር፣ 2 ኪሎ ፓስታ በ30 ብር እና 1 ፓኬት ክብሪት በ4 ብር ገዛች:: ወ/ሮ አልማዝ በጠቅላላው ስንት ብር ወጪ አደረገች?

ሐ. ሰብለወንጌል ተማሪ ነች:: ለመመዝገቢያ 40 ብር እና ለግማሽ ዓመት የትምህርት ክፍያ 250 ብር ከፈለች:: ሰብለወንጌል በጠቅላላ ስንት ብር ወጪ አደረገች?

የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

ሀ. ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ::

1. ሁሉም የኢትዮጵያ ብር ኖቶች በቅርጻቸው አንድ ዓይነት ናቸው::
2. የ100 ብር ኖት ከባለ 50 ብር ኖት ጋር እኩል ነው::
3. 100 ባለ 1 የብር ኖቶች በ2 ባለ 50 ብር ኖቶች ሊቀየሩ ይችላሉ::
4. 10 ባለ 100 ብር ኖቶች 1000 ብር ይሆናሉ::
5. 20 ባለ 5 ብር ኖቶች ከ1 ባለ 100 ብር ኖት ጋር እኩል አይደሉም::

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች የትክክለኛውን መልስ ፊደል ምረጡ::

1. 2 ባለ 100 ብር ኖቶች ጋር እኩል የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. 4 ባለ 50 ብር ኖቶች ሐ. 10 ባለ 10 ብር ኖቶች

   ለ. 8 ባለ አሥር ብር ኖቶች መ. 5 ባለ ሃምሳ ብር ኖቶች

2. ከ10 ባለ 10 የብር ኖቶች ጋር እኩል የሆነውን ለዩ::

   ሀ. 2 ባለ 50 ብር ኖቶች ሐ. 10 ባለ 5 ብር ኖቶች

   ለ. 4 ባለ 10 ብር ኖቶች መ. ሁሉም መልስ ነው::

3. ከሚከተሉት አንዱ የመገበያያ ገንዘብ ምድብ አይደለም::

   ሀ. ብር ለ. ሳንቲም ሐ. ጨው መ. ሀ እና ለ

4. 95 ብር ስንት ባለ 10 ብር ኖቶች እና ስንት ባለ 5 ብር ኖቶች ይኖሩታል? 95 ብር በስንት የባለ 5 ብር ኖቶች ይመነዘራል? 95 ብር በስንት የባለ አንድ ብር ኖቶች ይመነዘራል?

5. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስሉ::

   ሀ. 6 የ5 ብር ኖቶች ስንት የ1 ብር ኖቶች ይሆናሉ?

   ለ. 10 የ5 ብር ኖቶች ስንት የ1 ብር ኖቶች ይሆናሉ?

   ሐ. 4 የ50 ብር ኖቶች ስንት የ1 ብር ኖቶች ይሆናሉ?

   መ. 2 የ50 ብር ኖቶች ስንት የ10 ብር ኖቶች ይሆናሉ?

   ሠ. 4 የ100 ብር ኖቶች ስንት የ50 ብር ኖቶች ይሆናሉ?

   ረ. 6 የ50 ብር ኖቶች ከስንት የ100 ብር ኖቶች ጋር እኩል ይሆናሉ?

ምዕራፍ ስምንት

ጊዜ

8.1 ሰዓትን በግማሽና በሩብ አቆጣጠር መቁጠር

ተግባር 8.1

1. ቤተሰቦቻችሁ የቁርስ ሰዓት፣ የምሳ ሰዓት እንዲሁም የእራት ሰዓት መድረሱን በምን ያውቃሉ? ተወያዩ።
2. ከቤታችሁ ወደ ት/ቤት ስትጓዙ የሚወስድባችሁን ጊዜ የምትለኩበት መሳሪያ ምንድን ነው?
   - ተማሪዎች ወደ ት/ቤታችሁ የምትጓዙት በመኪና ወይስ በእግራችሁ?
   - በመኪና ከሆነ ስንት ሰዓት ወይም ደቂቃ ይወስድባችኋል?
   - በእግራችሁ ከሆነ ስንት ሰዓት ወይም ደቂቃ ይወስድባችኋል?

ከላይ በተወያያችሁት መሠረት ጊዜን ለመለካት የምንጠቀመው በዋነኛነት **ሰዓትና ደቂቃ** ነው።

ሰዓት ማለት ጊዜን በሰከንድ፣ በደቂቃ እና በሰዓት የሚለካ መሳሪያ ነው።


- የእጅ ሰዓት፣ የግድግዳ ሰዓት እና የጠረጴዛ ሰዓት ጊዜያችንን ለመለካት እንጠቀማለን።



የእጅ ሰዓት፣



ዲጂታል የእጅ



የጠረጴዛ

ተማሪዎች ከስዕሉ እንደምትመለከቱት በእያንዳንዱ ቁጥሮች መሀከል አምስት አምስት ጭረቶችን ታያላችሁ። ከአንዱ ቁጥር ማለትም ከ12 ብትነሱ እና ዙሩን ሙሉ ብትቆጥሩት 60 ታገኛላችሁ። ስለዚህ ደቂቃ ቆጣሪው ዘንግ አንድ ሙሉ ዙር ሲዞር የሰዓት ቆጣው ዘንግ አንድ ጭረት ይንቀሳቀሳል።

በዲጅታልም ሰዓት ብትመለከቱ የደቂቃ ቆጣሪው 60 ሲሞላ የሰዓት ቆጣሪው በአንድ ሰዓት ቁጥር ይጨምራል።

ቀጥለን የሰዓት፣ የደቂቃና የሴኮንድ ግንኙነትን እናያለን።

1 ሰዓት = 60 ደቂቃዎች

ምሳሌ፡-



ስንት ሰዓት ነው?

ሰዓትና ደቂቃ ቆጣሪው መለየት አለበት

የሰዓት ቆጣሪያችን 12ን ያመለክታል።

የደቂቃ ቆጣሪያችን 15ን ያመለክታል።

ስለዚህም 12 ሰዓት ከ15 ደቂቃ ላይ ያመለክታል ወይም 12 ሰዓት ከሩብ ነው እንላለን።

12፡15፡00

12 ሰዓት ከ15 ደቂቃ (12 ሰዓት ከሩብ)

አናሎግ	ሰዓቱ ሲነበብ	ዲጂታል
1. 	አሥራ አንድ ሰዓት =	
2. 	አሥራ ሁለት ሰዓት ከ25 ደቂቃ	
3. 	አንድ ሰዓት ከ15 ደቂቃ (አንድ ሰዓት ከሩብ)	

☺ አስታውሱ

1. 15 ደቂቃን ሩብ ሰዓት ብለን ስንጠራው 30 ደቂቃን ደግሞ ግማሽ ሰዓት ብለን እንጠራለን።
2. 45 ደቂቃን ሩብ ጉዳይ በማለት እናነባለን። ለምሳሌ 2:45 ሲነበብ ለ3 ሰዓት ሩብ ጉዳይ ወይም ሶስት ሰዓት ሊሆን 15 ደቂቃ የጎደለው በማለት እንገልጻለን።

መልመጃ-8ሀ

ሀ. የሚከተሉትን አናሎግ ሰዓቶች በማየት አንብቧቸውና በዲጂታል ሰዓት ሰዓቱንና ደቂቃን አመልክቱ።

	ዲጂታል ሰዓት		አናሎግ ሰዓት
1.		=	
2.		=	
3.		=	
4.		=	

ለ. የሚከተሉትን ዲጂታል ሰዓቶች በማየት አንብቢቸውና በአናሎግ ሰዓት ሰዓቱንና ደቂቃውን አስቀምጡ።

ምሳሌ፦	የሰዓት አነባበብ	ዲጂታል ሰዓት
	ስድስት ሰዓት ከሩብ	
1.	_____	 _____
2.	_____	 _____
3.	_____	 _____

8.2 ሰዓትና ደቂቃ

ተግባር 8.2

1. ተማሪዎች 30 ደቂቃ ስንት ሰዓት ነው?
2. 75 ደቂቃ ስንት ሰዓት ከስንት ደቂቃ ይሆናል? ውጤቱን በአናሎግ እና በዲጂታል ሰዓት በመጠቀም አመልክቱ።

ለምሳሌ፦

1 ሰዓት 60 ደቂቃዎችን ይይዛል። ይህ ሲባል በአናሎግ ሰአት የሰዓት ቆጣሪው 1 ሰዓት ሲጨምር የደቂቃ ቆጣሪው 60 ጊዜ ጠቅ ጠቅ በማለት አንድ ሙሉ ዙር ይዞራል ማለት ነው።

ስለዚህ 1 ሰዓት = 60 ደቂቃ

2 ሰዓት = 120 ደቂቃ

3 ሰዓት = 180 ደቂቃ

መልመጃ-8 ለ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ወደ ሰዓት ለውጡ። በምሳሌው መሠረት አስቀምጡ።

ምሳሌ፡-

1. 80 ደቂቃ ስንት ሰዓት ነው?

80 ደቂቃ = 60 + 20 ደቂቃ



አንድ ሰዓት ከ20 ደቂቃ



ሀ. 170 ደቂቃ = _____ ደቂቃ + _____ ደቂቃ





ለ. 180 ደቂቃ = _____ ደቂቃ + _____ ደቂቃ





ሐ. 90 ደቂቃ = _____ ደቂቃ + _____ ደቂቃ





መ. 150 ደቂቃ = _____ ደቂቃ + _____ ደቂቃ





የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃዎች

1. አበበ ከቤቱ ወደ ትምህርት ቤቱ ሲጓዝ 50 ደቂቃ ይወስድበታል። በተመሳሳይ አጓጓዝ አበበ ለደርሶ መልስ ጉዞው ስንት ደቂቃ ይወስድበታል? በሰዓት ሲገለፅስ?
2. 2 ሰዓት ከ45 ደቂቃ ስንት ደቂቃ ነው?
3. በአናሎግ የእጅ ሰዓት ላይ ከሁለቱ ዘንጮች ረዥሙ ዘንግ ምንን ይቆጥራል? አጭሩስ?
4. የሚከተሉትን ወደ ዲጂታል ሰዓት አቆጣጠር ቀይሯቸው።
   ሀ. 110 ደቂቃ
   ለ. 125 ደቂቃ
   መ. 45 ደቂቃ
   ሠ. 2 ሰዓት ከ35 ደቂቃ
5. የሚከተሉትን በአናሎግ የሰዓት ምስል አመላክቱ።
   ሀ. 1 ሰዓት ከ55 ደቂቃ
   ለ. 6 ሰዓት ከ15 ደቂቃ
   መ. 12 ሰዓት ከ10 ደቂቃ
   ሠ. ½ ሰዓት

ምዕራፍ ዘጠኝ

መረጃ አያያዝ እና ድርድር

መረጃ አያያዝ እና ድርድር

ተግባር 9.1

ተማሪዎች የአዝርዕት ዓይነቶችን፣ የጓሮ አትክልት ዓይነቶችን፣ የቤት ውስጥ እቃዎችን ዘርዝሩ። የሚመሳሰሉትን በአንድ ላይ በመዘርዘር መድቧቸው። የሚመሳሰሉበትን መንገድ አብራሩ።

9.1. ቀላል መረጃዎችን መሰብሰብ

ተማሪዎች መረጃዎችን ስታደራጁ ቀላሉ መንገድ በዓይነታቸው፣ በመጠናቸው፣ በተሰሩበት ቁስ ወይም በባህሪያቸው የሚመሳሰሉ መሆን አለበት።

ምደብ 1 (ፍራፍሬዎች)	ሎሚ	ብርቱካን	ሙዝ	ማንጎ	ፓፓዬ	አናናስ
ምድብ 2 (አዝርዕት)	ባቄላ	ስንዴ	ማሽላ	ሽምብራ	ጤፍ	በቆሎ

የቡድን ሥራ

በአንድ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚገኙ መገልገያ መሳሪያዎችን በመዘርዘር ከእንጨት የተሰሩ፣ ከሸክላ (ከአፈር) የተሰሩ፣ ከብረት የተሰሩ እና ከእንጨትና ከብረት ጥምረት የተሰሩ በማለት በምሳሌው መሠረት ሙሉ።

ምደብ 1	ምድብ 2	ምድብ 3	ምድብ 4
ከእንጨት የተሰሩ	ከሸክላ የተሰሩ	ከብረት የተሰሩ	ከእንጨትና ከብረት በጥምረት የተሰሩ
• ጠረጴዛ • _____ • _____ • _____ • _____	ሸክላ ድስት _____ _____ _____ _____	የብረት ድስት _____ _____ _____ _____	መደሻ _____ _____ _____

መልመጃ-9 ሀ

1. በክፍላችሁ ውስጥ የሚገኙ ወንድና ሴት ተማሪዎችን በመለየትና በስም በመዘርዘር በሁለት ምድብ መድቡ::
2. በክፍላችሁ ውስጥ የሚገኙትን ቁሳቁሶች ጎነ አራት፣ ጎነ ሦስት እና የክብ ቅርጽ ያላቸውን በመዘርዘር በሦስት ቦታ መድቡ::
3. የሚከተሉትን የእንስሳት ዝርዝር በማጤን መድቡ፤ ሠንጠረዡንም ሙሉ::

አንበሳ	ውሻ	በግ	ዋልያ	ድመት	ወፍ
ዝንጀሮ	ላም	በቅሎ	ቀይ ቀበሮ	ዶሮ	
ዝሆን	ነብር	ጎሽ	በሬ	አሞራ	
ጦጣ	አነር	ሚዳቋ	ፈረስ	አህያ	

የቤት እንስሳት	የዱር እንስሳት	በክንፍ በራሪ

9.2. የቀላል መረጃ ሰንጠረዥ

ተግባር 9.2

1. ተማሪዎች የአናፂ፣የህክምና እና የግብርና ባለሙያዎች ሥራቸውን ለማከናወን የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎች በመዘርዘር መድቧቸው::
2. እናንተ ለትምህርት የሚያስፈልጓችሁን መሳሪያዎች ዘርዝሩ:: ከዘረዘራችሁ በኋላ በሦስት በተለያዩ ምድቦች ለመመደብ ሞክሩ::

ምሳሌ:-



የቁም መጥረጊያ



መዶሻ



ቁልፍ



ፊሽካ እስኪርፕቶ



አካፋ



ደወል



መጋዝ



እርሳስ

እነዚህን መሳሪያዎች በቀላሉ በመረጃ ሰንጠረዥ እናስቀምጣቸው። የህንፃ መሳሪያዎች እና የትምህርት መሳሪያ ዕቃዎች በማለት በሰንጠረዡ አሳዩ።

የህንፃ መሳሪያ	የትምህርት መሳሪያዎች
• ቁልፍ • መዶሻ • የቁም መጥረጊያ • መጋዝ • አካፋ	• እስኪርፕቶ • እርሳስ • ደወል • ፈሽካ

መልመጃ-9 ሀ

በምሳሌው መሠረት መድቡ።

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቁሶች ፈሳሽና ጠጣር በማለት በሠንጠረዥ አደራጁ።

ወተት	ውኃ	ግድግዳ	ድንጋይ
ባትሪ ድንጋይ	ዘይት	ወንበር	መዶሻ

2. ቀጥሎ የተሰጡት የቁሳቁሶች ዝርዝር ከሥር በተሰጠው ሠንጠረዥ አደራጁ።


- እንቁላል	- ወተት	- ምስር	- ባቄላ	- በቆሎ	- በርበሬ	- ድንች
- ስጋ	- ሽንኩርት	- ስንዴ	- ጐመን	- ቲማቲም	- ብርቱካን	-
- መፅሐፍ	- ወንበር	- ደብተር	- እስኪርቢቶ	- ጠመኔ		

ጥራጥሬ	የእንስሳት ተዋፅኦ	የፅሕፈት መሳሪያዎች	የጓሮ አትክልት

9.3 የቁጥሮችና የቅርፃ ቅርጾች ቀላል ድርድር

ተግባር 9.3

1. ተማሪዎች የቁጥሮችን ቅደም ተከተል ሁለት ሁለት በመዝለል መግለጽ ትችላላችሁን?
2. የሚከተሉትን ቅርጾች ድርድር በመመልከት ክፍት ቦታዎችን ሙሉ::



_____፣_____፣ ____

- የቁጥሮችንና የቅርፃ ቅርጾችን ቀላል ድርድር እንደ አጀማመራቸው በመመልከትና በማጤን መደርደር ይቻላል::

ለምሳሌ፡-



_____፣ ____ ፣____ባዶ ቦታውን ሙሉ::

መፍትሔው 

መልመጃ-9 ሐ

I. የሚከተሉትን ነገሮች ቀላል ድርድር በማጥናት ባዶ ቦታውን ሙሉ ወይም ቀቡ::

ሀ. 

_____፣_____፣_____፣_____::

ለ. 2፣ 4፣ 6፣ _____፣ _____፣_____፣14፣_____ ፣_____፣20


ሐ. 0፣ 3፣ 6፣ 9፣ _____፣ _____፣ 18፣ 21፣ _____፣ 27

መ. 

፣_____፣_____፣_____::

ሠ. 

_____፣_____፣_____::

ረ. 

_____፣ _____ ፣_____፣

የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

ሀ. ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ::

1. ሁሉም የቤት ውስጥ እቃዎች ተመሳሳይ አገልግሎት አላቸው::
2. የተለያዩ መረጃዎችን ስናሰባስብ በአንድ ቦታ ማከማቸት ጠቃሚ ነው::
3. መረጃዎችን በመጠናቸው፣ በአይነታቸውና በባህሪያቸው ለይቶ ማደራጀት ጠቃሚ ነው::
4. ቀላል መረጃዎችን በሰንጠረዥ ማደራጀቱ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው::
5. የተለያዩ ቀርጽ ያላቸውን ቁሶች በየቅርፃቸው መደርደር አስፈላጊ ነው::

ለ. የሚከተሉትን የቁጥርና የቅርፃቅርጽ ድርድር ወይም ፓተርን አሟሉ::

1. 0፣ 4፣ 8፣ _____፣ _____፣ 20፣ 24፣ _____፣ 32፣ 36፣ _____፣ 44

2. ፣ _____፣ _____::

_____፣ _____፣ _____፣ _____::

ሐ. የሚከተሉትን ነገሮች ባህሪይ በማጤን መድቡአቸው፤ በሠንጠረዥም አሳዩ::

ብርቱካን	ፓስታ	ትርንጎ
በቅሎ	መኮረኒ	አቡካዶ
መንደሪን	ሩዝ	በግ
ፍየል	ሙዝ	ስኳር
ዶሮ	ፓፓያ	ጨው